# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 114 ታኅሣሥ 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# መንግሥት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት ያደረገው ጥረት የሚመሰገን ነው



ዶክተር አረጋዊ በርሄ

ፎቶ - አጋፔ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት ያደረገው ተደጋጋሚ ጥረት የሚመሰገን ነው ሲሉ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ተናገሩ፡፡

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ዶክተር አረጋዊ በርሄ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት በጦርነት ችግሮችን መፍታት ዘላቂ መፍትሔ አይሆንም፤ ዘላቂ መፍትሔ ልናገኝ የምንችለው በሰላም እና በመነጋገር መቋጨት ስንችል ነው።

ኢትዮጵያ በትንሹ ለሁለት ዓመታት በግጭት ስትታመስ በመቆየቷ ሕዝቡ ላይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊ እና ሌሎችም ብዙ ጉዳቶችን አድርሶበታል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በመሆኑም ይሄ ግጭት በሰላም መቋጨቱ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ማንኛውም ሰው በደስታ ሊቀበለው የሚገባ ተግባር ነው፤ እኛም በደስታ ነው የተቀበልነው ብለዋል፡፡

መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ባለፉት 10 ዓመታት ወደ ካዳስተር ሥርዓት የገባው የመሬት ይዞታ ከ25 በመቶ አላለፈም

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ላለፉት 10 ዓመታት ወደዘመናዊ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ምዝገባ ካዳስተር ሥርዓት የገባው የመሬት ይዞታ ከ25 በመቶ እንዳላለፈ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት

ባለፉት 10 ዓመታት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ከትላንቱ ጉዳት የነገ ተስፋችን ስለሚበልጥ ለቀጣይ ልማታችን ልንበረታ ይገባል”

- አቶ ከበደ አሰፋ

የቀድሞ መቀሌ ከተማ መንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ኃላፊ

ገጽ 4

## ብልጽግና ብቃት ያላቸው ተቋማትን በመገንባት የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዳማ፡- ብልጽግና ፓርቲ ነፃ፣ ገለልተኛና ብቃት ያላቸው ተቋማትን በመገንባት የወጣቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየሠራ መሆኑን የፓርቲው ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለፁ።

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አንደኛ መደበኛ ጉባዔ “ለኢትዮጵያ እና ለአፍሪካዊ ብልጽግና የሚተጋ ወጣት” በሚል መሪ ሃሳብ በትናንትናው ዕለት የመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱን አካሂዷል።

በጉባዔው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የዋና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ፤ ብልጽግና ነፃ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው ተቋማትን በመገንባት ላይ መሆኑን ጠቅሰው፤ ነፃ፣ ገለልተኛና ብቁ ተቋማት መገንባታቸው ከማንም በላይ የዛሬና የነገ ወጣቶችን የሚጠቅም ነው ብለዋል።

“ብልጽግና ፓርቲ በለውጥ ውስጥ ተጸንሶ ለለውጥ የተወለደ የዛሬና የነገ ወጣቶች ፓርቲ ነው” ያሉት አቶ አደም፤ በሥሩ ያሉት ወጣቶችም የነገ አገር ተረካቢ ብቻ ሳይሆኑ የዛሬ አገር ገንቢዎች ናቸው ሲሉ ገልፀዋል። ወጣቶች ኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለመትከል በምታደርገው ጥረት፣ በአገር ግንባታና በብሔራዊ መግባባት ዙሪያ በሚከናወኑ ተግባራት ግንባር ቀደም ተሳታፊና ተዋናይ


ብልጽግና ብቃት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ አደም ፋራህ


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት



Packing & Moving
ኩሊ የእቃ አስተላላፊ
Kuli Freight Forwarding
- የቤትና የቢሮ እቃዎችን ደህንነታቸውን በጠበቁ የማሸጊያ እቃዎች በመጠቀም የማሸግና የማጓጓዝ አገልግሎት
- በአደራ ተቀብሎ ማድረስ
- ለገቢና ወጪ እቃዎች የጉምሩክ /ትራንዚት አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
- እቃዎችን እንልካለን ከውጭ የተላኩትንም እንቀበላለን፡፡
- ከአዲስ አበባ ወደ ክልሎች ከክልሎች ወደ አዲስ አበባ
www.kulilogistic.com
0911010315
0930807777

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565





አቶ መሐመድ አሚን የሱፍ

# በአካባቢው ሰላም በመረጋገጡ ኢንቨስተሮች ወደ ሥራ እየተመለሱ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ኮምቦልቻ፡- በሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው ጦርነት በሰላም በመቋጨቱና በአካባቢው ሰላም በመረጋገጡ ቀድሞ ከአካባቢው ሄደው የነበሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሥራ እየተመለሱ መሆኑን የኮምቦልቻ ሪጂኦ ፖሊቲያን ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊቲያን ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ መሐመድ አሚን የሱፍ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፥ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ባለሃብቶች ከሥራቸው ተፈናቅለው ሠራተኞችም ተበትነው ነበር። ይሁንና በሕወሓት እና በፌዴራል መንግሥት መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት በርካቶች ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እየተመለሱ ነው።

እንደ ከንቲባው ገለጻ፥ "ጦርነት እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። ቀጥታ ወረራው አማራ እና አፋር ክልሎች ላይ ያነጣጠረ ነበር። ከአማራ ክልል ደግሞ ወሎ በጣም መጎዳቱ ይታወቃል። ሆኖም ሰላም ማስቀደም ተገቢ ነው። ጦርነት በጦርነት ብቻ አይቋጭም። ድርድር መደረጉና ሠላም መምጣቱ ትልቅ ፋይዳ አለው። ጦርነቱ እንዲቀጥል የሚፈልግ ካለ የኢትዮጵያ ጠላት ነው። ነገር ግን ሰላምና ድርድሩ የእውነት እንዲሆን" እንፈልጋለን ብለዋል።

ይህ ሰላም ለእኛ ትልቅ ዕድል ነው ያሉት አቶ መሐመድ አሚን፤ ሰላም ከሆነ ስለ ጦርነት ማሰብ እናቆማለን። ገንዘብ ስናወጣ የነበረው ለሀገር መከላከያ ሠራዊትና ለጥምር ጦሩ ደጀን ለመሆን ነበር። ጦርነት ባለበት አካባቢ ኢንቨስትመንት አይመጣም። የትግራይ ሕዝብና የወሎ ሕዝብም በመልክዓ ምድርና በአኗኗሩም የሚቀራረብና የሚዋሰን ነው። በመሆኑም የወሎና የትግራይ ሕዝብ ተመልሶ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ሕይወቱ እንዲተሳሰር እንፈልጋለን። በምሥራቁ ክፍልም የአፋር፣ የወሎና የትግራይ ሕዝብ በማኅበራዊ ሕይወት የሚተሳሰር ነው። እኔም እንደ ዜጋ ለዚህ ሰላም የሚከፈለውን ሁሉ መስዋዕትነት ለመክፍል ዝግጁ ነኝ። ስለዚህ ሰላሙ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው። በጦርነቱ ብንጎዳም ከትግራይ ሕዝብ መስተጋብራችን መቀጠል እንፈልጋለን። እኔም ከልቤ እደግፈዋለሁ። በመሆኑም ከትግራይ ሕዝብ ጋር ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር እንፈልጋለን ብለዋል።

የኮምቦልቻ ሪጂኦፖሊቲያን ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪና ኢንቨትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ ሐብታሙ ኃይሌ በበኩላቸው፤ በኮምቦልቻ ከተማ በጦርነቱ በኢንዱስትሪዎች ላይ ትልቅ ጉዳት ደርሷል። ከኢንዱስትሪዎችም በተጨማሪም አምራች ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በርካቶችም ከውጭ ሀገራት ያስመጡዋቸው ጥሬ ግብዓቶች ውድመት እና ብልሽት ደርሶባቸዋል። ይሁንና መንግሥት ሰላም እና የሀገር ጥቅምን በማስቀደም ችግሮችን በድርድር ለመቋጨት በመወሰኑ ከተማዋ ወደ ቀድሞ የኢንቨስትመንት ኮሪደርነቷ እየተመለሰች ነው።

ጉዳት ደርሶባቸው የነበሩ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና በመከታታል ወደ ሥራ እየተመለሱ ሲሆን፤ የውጭ ኢንቨስተሮችም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ሥራቸውን እየጀመሩ መሆኑን አቶ ሐብታሙ አረጋግጠዋል።

# ባህላዊ የግጭት አፈታት- የዘላቂ ሰላማችን ዋስትና

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያውያን ለብዙ ዘመናት አብሮ በመኖር፣ አብሮ በመብላት፣ ችግሮቻቸውን ያለማንም ጣልቃገብነት በመፍታት የጎለበተ ባሕላዊ ሥርዓት አላቸው፡፡ በተለይ ባሕላዊ የግጭት ሥርዓቶቻችን በደም የጨቀዩ ግንኙነቶችን ጭምር በማጥራት ሃገር በተረጋጋ ሥርዓት እንድትኖር ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡

ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ከመደበኛ የፍርድ አሰጣጥ ጎን ለጎን ለፍትሕና ለሰላም መስፈን ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡ ኢትዮጵያም በአገር ሽማግሌዎች እና በባሕላዊ መሪዎች ተፅዕኖ ፈጣሪነት የሚመሩ ሽንጎዎችና የእርቅ ሥርዓቶች ያላት ሀገር ነች። ነገር ግን ይህ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የግጭት አፈታት ሥርዓት እያለ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ አካባቢዎች በዜጎች መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች የሚከሰቱ ውድመቶች ማየት በእጅጉ ያማል፡፡ አለመግባባቶቹ በባሕላዊ ሽምግልና መፈታት ሲገባቸው በተቃራኒው ጥቃቅን ግጭቶች ተባብሰው ለሰው ሕይወት መጥፋት፣ ለንብረት መውደምና ለዝርፊያ ምክንያት እየሆኑ መጥተዋል፡፡

ዶክተር መልሰው ደጀኔ በአዋሳ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት እንዲሁም የልማት ጥናት ረዳት ፕሮፌሰርና ተመራማሪ ናቸው። "በኢትዮጵያ የባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት ቢኖርም እምብዛም የጎለበተ አይደለም" ይላሉ። በሚከሰቱ አለመግባባቶች በባሕላዊ የግጭት አፈታቱ ሥርዓት ክብደት ተሰጥቶ ቢሠራ ኖሮ እንደ ሀገር የተከፈለው ዋጋ በእጅጉ ይቀንስ ነበረ፡፡ መንግሥት ለፍትሕ ሥርዓቱና በጥቅሉ ለሕግ ያስቸገሩ ጉዳዮች በባሕል መሪዎችና ሽማግሌዎች ትኩረት በመስጠት አለመግባባቶቹ የከፋ ችግር ሳያስከትሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

"የባሕላዊ ግጭት አፈታት ሥርዓት አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት የጋራ አሸናፊዎች መስተጋብር ነው" የሚሉት ዶክተር መልሰው፤ አጥፊም ሆነ ተጠቂው አሸንፈው የሚወጡበት ሥርዓት እንደሆነና ፍርድ ቤት በመሄድ ፍትሕ ማግኘት ቢቻልም "የቂም በቀለኝነት አዙሪት" የማያቃልል በመሆኑ ባሕላዊው የግጭት አፈታቱ ግን ሙሉ እርቅና ግጭትን የማስወገድ አቅም አለው ይላሉ፡፡

አቶ ተስፋዬ ደነቀ የሲዳማ ብሔር የሀገር ሽማግሌ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ በሲዳማ ክልል ባሕላዊ የግጭት አፈታት ተመራጭ ሲሆን በግለሰብም ሆነ በቡድን ለሚነሱ አለመግባባቶች በሽምግልናና በልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች መፍትሔ ይሰጣል።

የሀገር ሽማግሌው አቶ ተስፋዬ ደነቀ፤ ይህንን ማድረግ የሚችል ባሕላዊ አቅምና ሥርዓት ማጎልበት እና ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል በማለት አሁን በተለያዩ አካባቢዎች ለሚነሱ ግጭቶችና ለሚደርሱ ጥፋቶች መፍትሔው በእጅ እንዳለ ነው የሚናገሩት። እርሳቸውን ጨምሮ ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የመጡ የአገር ሽማግሌዎችም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በባሕላዊ እሴቶች እና እውቀቶች ለመፍታት እንዲያስችላቸው የጋራ የባሕል መሪዎች ምክር ቤት ለማቋቋም ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ሌላኛው የሀገር ሽማግሌ አቶ አዳነ አዳም ሰገድ በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ ነዋሪ ናቸው። በአማራ ክልል ግጭትና አለመግባባት ሲከሰት ለመፍታት የሚያስችል የተለያየ የሽምግልና ሥርዓት እንዳለ ይናገራሉ። በዚህ መሠረት ችግሮች ሲቃለሉ መቆየታቸውንም ይገልፃሉ። ይህንን ባሕላዊ ሥርዓት ማጎልበትና አሁን አሁን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚከሰቱ አለመግባባቶች መፍትሔ ለማምጣት መሥራት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

"የቀድሞ አባቶቻችን በራሳቸው ባህል፣ ወግና ሥርዓት አለመግባባቶችን የሚፈቱበት ፍትሕና እውነትን የሚያስታርቁበት መንገድ ነበራቸው" የሚሉት አቶ አዳነ፤ይህ ልምድ አሁን እየደበዘዘና ተቀባይነት እያጣ መምጣቱን ይናገራሉ። ሥርዓቱን ዳግም መመለስ፣ ሰላም ማስፈን፣ ፍትሕና እውነትን ማረጋገጥ የአገር ሽማግሌዎች፣ የባሕል መሪዎች እንዲሁም ከመንግሥት የሚጠበቅ የቤት ሥራ መሆኑን በአስተያየታቸው ላይ ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ከ85 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ በርካታ የእርቅ፣ አለመግባባትን መፍቻ እንዲሁም ግጭትን ማስወገጃ ባሕላዊ ሥርዓት አለ። ከዚህ ውስጥ የጋሞ፣ ሲዳማ፣ የአማራ የኦሮሞና የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ተጠቃሽ ናቸው።







# ባለፉት ሦስት ዓመታት አንድ ሺህ ለሚበልጡ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፈቃድ ተሰጥቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-ባለፉት ሦስት ዓመታት ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው የቡና ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል። ባለፉት ሦስት ዓመታትም ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፈቃድ አግኝተዋል።

የቡና ላኪነት ፈቃድ ከወሰዱት አርሶ አደሮች መካከል ከ100 በላይ የሚሆኑ ቡናቸውን በቀጥታ ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርቡም ገልጸዋል።

በዘንድሮ በጀት ዓመት 360 ሺህ ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 2 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ባለስልጣኑ ባለፉት አራት ዓመታት የሪፎርም ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል ያሉት ምክትል ዳሬክተሩ የቡና ምርት ጥራትን ማስጠበቅ፡ የግብይት ሥርዓቱን ማዘመንና በምርቱ ላይ እሴት መጨመር ምርታማነቱን ማሳደግ መቻላቸውን ተናግረዋል።

በሪፎርሙ በቡና ግብይት ላይ ከፍተኛ እድገት በማምጣት የውጭ ምንዛሪ እንዲጨምር ተደርጓል ያሉት ኃላፊው ለአብነትም ባለፈው በጀት ዓመት 302 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በመላክ አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን አስታውሰዋል።

የሪፎርም ሥራዎች መተግበር ከጀመሩ ወዲህ ባሉት አራት ዓመታት ወደ ውጭ የተላከ የቡና ምርት በ104 ሺህ ቶን እድገት ማስመዝገቡንም ነው የገለጹት።

ባለስልጣኑ የዓለም የቡና ገበያ ተለዋዋጭነትን መሠረት በማድረግ ተጨማሪ የገበያ መዳረሻዎችን



የማፈላለጉን ሥራ በትኩረት እያከናወነ መሆኑን እንደ ኤዥያ ባሉ አካባቢዎች አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት እንቅስቃሴ መጀመሩን መግለጻቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# ክልሉ በ49ሺህ ሔክታር መሬት ላይ የበጋ መስኖ ልማት እያከናወነ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- በ49ሺህ ሔክታር መሬት ላይ የበጋ መስኖ ልማት እያካሄደ መሆኑን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስታወቀ፡፡ ለመስኖ ልማቱ 420 የውሃ መሳቢያ ጄኔሬተሮችና 60 ትራክተሮች ቀርበዋል፤ በዚህም ከመስኖው 10 ሚሊዮን 500ሺህ ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ክልሉ አስታውቋል።

የክልሉ ግብርናና ተፈጥሮ ኃብት ቢሮ ኃላፊ አቶ ባባክር ኸሉፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ሰፊ የውሃ ሀብት ባለባቸው ወረዳዎች በ49ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የበጋ መስኖ ልማት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

ለመስኖ ልማቱ ዋናው ግብዓት የሆኑ የዘር፣ የምርጥ ዘርና ማዳበሪያ አቅርቦት መከናወኑን የገለጹት አቶ ባባክር፤ ለመስኖ ልማቱ የሚረዱ የሜካናይዜሽን መሣሪያዎች አቅርቦትም ቀድሞ መጠናቀቁን ጠቁመዋል፡፡

የመስኖ ልማቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ 420 የውሃ መሳቢያ ጄኔሬተሮችና 60 ትራክተሮች መቅረባቸውን የተናገሩት ኃላፊው፣ ትራክተሮቹና ጄኔሬተሮችን ለአርሶአደሮች መሰራጨት መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳ ዞን ውስጥ ካሉት ዘጠኝ ወረዳዎች በስድስቱ የመስኖ ልማቱ ተጀምሯል። በመተከል ዞንም ካሉት ሰባት ወረዳዎች ውስጥ በስድስቱ መስኖ ሥራው ተጀምሯል ብለዋል፡፡

የመስኖ ልማት ሥራው በዋናነት በበጋ ሰንዴ ምርት ላይ ያተኮረ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከስንዴ በተጨማሪ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ሌሎች ሰብሎችም እንደሚለሙ አስረድተዋል።

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በአሶሳና መተከል ዞኖች ብቻ 11 ሺህ ሔክታር እንደሚለማ ጠቁመዋል፡፡

ኃላፊው እንዳስታወቁት፣ በባምባሲ ወረዳ ደግሞ 1913 ሄክታር ማሳ ለማልማት ታቅዶ እስካሁን 1305 ሄክታር መሬት ላይ መሬት የማዘጋጀት፣ ማሳውን በዘር የመሸፈንና የተለያዩ ሥራዎች ተከናውነዋል።

በተጨማሪም በተለያዩ ወረዳዎች ላይ የዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ 30ሺህ ሄክታር የሚሸፍን የበቆሎ መስኖ ልማት እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

በአጠቃላይ ከክልል የበጋ መስኖ ልማት ሥራ 10 ሚሊዮን 500 ሺህ ኩንታል ምርት ይጠበቃል ብለዋል።

አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት በተፈጠረላቸው የካማሺ ወረዳና የማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳዎችም የመንግሥት አመራሮችና ባለሙያዎች ወደ ሥራ እየተመለሱ በመሆናቸው በተጨማሪነት የበጋ መስኖ ልማቱ የሚከናወንባቸው አካባቢዎች እንደሚሆኑ ገልጸዋል።

# ዲያስፖራው በዘላቂነት ሀገሩን የሚጎበኝበት አሠራር ሊዘረጋ ነው

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- ባለፈው የገና በዓል ዲያስፖራው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተደረገለትን ሀገራዊ ጥሪ ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት በመምጣቱ ያደረገውን ሀገራዊ ሁለንተናዊ ተሳትፎ በዘላቂነት ለማስቀጠል በየዓመቱ ሀገሩን የሚጎበኝበት አሠራር ሊዘረጋ መሆኑን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የዛሬ ዓመት ለዲያስፖራው ወደ ሀገር ቤት ጥሪን ያደረጉት ሀገራችን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በነበረችበት ወቅት ነው።

በዚህም የተደረገለትን ሀገራዊ ጥሪ ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት የመጣው ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዲያስፖራ በርካታ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ፤ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ አስተዋፅዖችን ለሀገሩ ማበርከት መቻሉን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፣ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ የነበረው ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲለዝብ ከማስቻል ጀምሮ ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር እና የኢትዮጵያውያን ኅብረት ኃይል መሆኑን እንዲሁም ኢትዮጵያ ሰላማዊ ሀገር መሆኗን ማረጋገጥ እንዳስቻሉ ጠቁመዋል፡፡

በወቅቱም በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ እንደሚባለው ለሕልውና አስጊ ሳይሆን በሐሰት ፕሮፖጋንዳ የሚካሄድ የስም ማጥፋት መሆኑንና ኢትዮጵያ በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኗን አሳይተዋል ብለዋል ።

ከዚህም ባለፈ በጦርነቱ ምክንያት በአፋርና አማራ ክልሎች ጉዳት ደርሶባቸው በችግር ውስጥ የነበሩ በርካታ ወገኖቻቸውንም በመጎብኘት መደገፍ መቻላቸውን የገለጹት አቶ ወንድወሰን፤ ኢትዮጵያውያን የራሳችንን ችግር በራሳችን መፍታት እንደምንችል ከማሳየት ጀምሮም የውጭ ጣልቃ ገብነት እንዲቆም ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል ብለዋል።

ዲያስፖራው ጥሪውን ተከትሎ ወደ ሀገር ቤት በመምጣቱ ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ኢኮኖሚው ፈሰስ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ ጥሪው የታሰበውን ዓላማ አሳክቶ ባለፈው ገና ቢጠናቀቅም ዘንድሮ ይሄን የዲያስፖራውን ለሀገር የሚደረግ አስተዋፅዖና ሁለንተናዊ ተሳትፎ አጠናክሮ በዘላቂነት ለማስቀጠል ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል ።



**አቶ ወንድወሰን ግርማ**

ዕቅዱ ዲያስፖራው በየዓመቱ ወደ ሀገር ቤት በመምጣት በዘላቂነት አገሩን የሚጎበኝበት መርሐ ግብር የሚዘረጋበት መሆኑንም ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

መርሐ ግብሩ ዲፕሎማሲያዊ፤ማኅበራዊ፤ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎችን መሠረት ያደረገ እንደሆነም ጠቁመዋል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለዲያስፖራው በታላቁ ቤተ መንግሥት የራት ግብዣ ባደረጉበት ወቅት ‹‹ልጆቻችሁንም እንፈልጋቸዋለን›› ሲሉ መልዕክት ማስተላለፋቸውን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ ይሄንኑ ዘላቂ መርሐ ግብር የዲያስፖራው ልጆች የትምህርት እረፍት በሚያደርጉበት የክረምት ወቅት እንዲጀመር መታሰቡንና ለዚህ ስኬት ይረዳም ዘንድ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ተግባሩ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የሚመራ የራሱ ኮሚቴ የተዋቀረለት መሆኑንም ገልፀዋል።

ዲያስፖራው አገሩ ችግር ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ በመንግሥት በሚደረግ ጥሪ ብቻ ሳይሆን በተመቸው ጊዜ ሁሉ ወደ ሀገር ቤት ብቅ በማለት ሀገሩንና ወገኑን መጎብኘት የሚያስችል አሠራር እንደሚዘረጋም አቶ ወንድወሰን ተናግረዋል፡፡

# መገናኛ ብዙኃን የሰላም ስምምነቱን የሚያጠናክሩ አጀንዳዎች ቀርጸው ሊሠሩ ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- መገናኛ ብዙኃን የሰላም ስምምነቱን ዘላቂነት የሚያጠናክሩ አጀንዳዎች ቀርጸው ሊሠሩና ማኅበረሰቡን ሊያነቁ እንደሚገባ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን መምህራን አስታወቁ።

በጂማ ዩኒቨርሲቲ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ጌታቸው ጥላሁን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የተጀመረው ሀገራዊ የሰላም ስምምነት ቀጣይነቱ የተረጋገጠ እንዲሆን ሁሉም ሚዲያዎች ትኩረት አድርገው ማኅበረሰቡን ያሳተፈ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

መገናኛ ብዙኃኑ በሀገሪቱ የተጀመረውን የሰላም ስምምነት ቀጣይነት እንዲኖረው ከማድረግ አኳያ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ሊያጠናክሩ የሚችሉ አጀንዳዎች ላይ ሰፊ የአየር ሰዓትና የሕትመት ቦታ መስጠት ይገባቸዋል ብለዋል።

በተጨባጭም በግጭት ውስጥ የነበሩትን የማኅበረሰብ ክፍሎች በማወያየት በግጭቱ ወቅት ከነበረው ስሜትና ሁኔታ እንዲወጡ የሚረዱ አጀንዳዎች ላይ ማተኮር አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ጌታቸው ገለጻ፤ መንግሥትም መገናኛ ብዙኃኑ በሚቀርጿቸው አጀንዳዎች ላይ እንዲሁም ማኅበረሰቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ላይ ተገቢውን ምላሽና ማብራሪያ በመስጠት መረጃ የማቅረብ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት።

ሚዲያዎች ሰላምን የሚሰብኩ አጀንዳዎችን በብዛት መፍጠር አለባቸው። በሰላም ሂደት ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትሩፋቶችን ለማጠናከር ትኩረታቸው አንድነትና ፍቅርን በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

በዓለም ላይ ያሉ አስደሳች ነገሮችን ሁሉ ማድረግ የሚቻለው በሰላም መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ጌታቸው፣ ሰላም ሲኖር ሀገር ማደግ ይችላል፣ ሰዎች በነጻነት መወያየት መግባባት እንደሚችሉ አመላክተዋል።

በሀገሪቱ ልዩነቶች፣ አጀንዳዎችና ታሪኮች በጣም ሰፊና ውስብስብ እንደሆኑ ዶክተር ጌታቸው አንስተው፤አሁን የተጀመረውን ሰላም በመጠቀም በሰከነ መንፈስ በመወያየት የልዩነቶች ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ለመፍታት ሚዲያ ትልቁን ድርሻ ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በዚህ ወቅት ስለ ሰላም ሰፊ ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ጌታቸው፤ ሚዲያዎች ማኅበረሰቡን በማንቃት፣ የመንግሥት አካላትንና ፖለቲከኞችን የሚሞግቱ አጀንዳዎችን በመቅረጽ እና መድረክ በማመቻቸት የማወያየት ሥራ ሊሠሩ ይገባቸዋል።



**ዶክተር ጌታቸው ጥላሁን**

በግጭት ውስጥ የነበሩትን የማኅበረሰብ ክፍሎች አንድ ማድረግ ላይ በትኩረት እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የተራራቀውን ማኅበረሰብ ከማገናኘት አንጻር ሚዲያዎች ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው የገለጹት ዶክተር ጌታቸው፤ ጦርነቱ ማኅበረሰቡ ላይ ያመጣቸውን መጥፎ ጠባሳዎችን በመርሳት በተጀመረው ሰላም ተጠቃሚ የሚሆንበት ጉዳይ ላይ እንዲወያዩና እንዲነጋገሩ መድረክ ማመቻቸት አለባቸው ሲሉ ጠቁመዋል።

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናትና ጋዜጠኝነት መምህር እና ተመራማሪ ዶክተር መልሰው ደጀኔ በበኩላቸው፤ የሚዲያ የመጀመሪያው ሥራ ማስተማር ነው። በመሆኑም ሚዲያዎች ሰላምን ለማኅበረሰቡ በማስተማር ከሰላም ተጠቃሚ ማድረግ አለባቸው ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

ሚዲያዎች በግጭት ውስጥ የነበሩ ማኅበረሰቦችን ወደ ዘላቂ ሰላም ሊያሸጋግሯቸው የሚችሉ ዘገባዎችን በእውነታ ላይ ተመሥርተውና ሚዛናዊ ሆነው ሊዘግቡ እንደሚገባቸወ የጠቀሱት ዶክተር መልሰው ፣ ሚዛናዊ ዘገባዎችን በማስተላለፍ ሀገራዊ ሰላሙን ዘላቂ ማድረግ አለባቸው ብለዋል።

በግጭቱ አከባቢ የነበሩ የትግራይ፣ የአማራና አፋር ሕዝቦችም የጦርነት አስከፊነት መደገም እንደሌለበት በልምድና በተግባር ያውቁታል ያሉት ዶክተር መልሰው፤ ሚዲያዎች በአከባቢው በመሔድ ጦርነት አስከፊ እንደሆነ ከማኅበረሰቡ ልምዳቸውን በመቀበል ለሌሎች በማካፈል ሰላምን ዘላቂ ማድረግ አለባቸው ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# በእናቶች እና ጨቅላ ሕጻናት ሞት ቅነሳ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የጤና ባለሙያዎችን ስልጠና በማስፋት እና አገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን በእናቶች እና ሕጻናት ሞት ቅነሳ ላይ አበረታች ውጤት መመዝገቡን ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ እንደገለጹት፤ የእናቶች እና የጨቅላ ሕጻናት ሞት ለመቀነስ ባለፉት ዓመታት የጤና ባለሙያዎች ስልጠና በማስፋፋትና አገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን ረገድ ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በቅንጅት በርካታ ሥራዎች ተሠርቷል። በተሠራው ሥራም አበረታች ውጤት ተመዝግቧል።

ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ሽፋን መቶ በመቶ ለማድረስ ማቀዷን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት የክትባት ሽፋን መቶ በመቶ ለማድረስም መታቀዱንም አክለው ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የጤናውን ዘርፍ እቅድ ለማሳካት ጠንካራና ፍትሐዊ የጤና ሥርዓትን ለመገንባት የጋራ ጥረትና ተጨባጭ እርምጃ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ሊያ፤ ለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርጾ ተግባራዊነታቸው ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር በትብብር እየሠራ እንደሚገኝና እንደሀገር ሁሉን አቀፍ፣ ፍትሐዊ እና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎትን ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ የትብብር ሥራዎች ይበልጥ መጠናከር አለባቸው ብለዋል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ዶክተር ደበበ ባሩድ በበኩላቸው፣ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ገንዘብ ስጋት ሳይሆንበት መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ያለምንም እክል ማግኘት መቻል አለበት ካሉ በኋላ ይህንን እውን ማድረግ ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ነው ብለዋል።

ለስኬታማነቱም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው ከጤና ሚኒስቴር እና ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ጥናቱን የጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ከዓለም አቀፍ ካውንት ዳውን 2030 የጥናት ቡድን ጋር በመተባበር ያጠናው ሲሆን በሪፖርቱ የእናቶች እና ጨቅላ ሕጻናት ሞት ቅነሳ በፈረንጆቹ ከ1990 እስከ 2019 እንዲሁም ከ2016 እስከ 2020 የጤና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም የጥናት እና ምርምር ግኝቶች የሚያብራራ ነው። በጥናቱም በኢትዮጵያ የጤና ሥርዓት ባለፉት አስርተ ዓመታት ከፍተኛ ለውጥ ማምጣቱ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ የ2030 ዕቅዶች ከ100 ሺህ ሰዎች ውስጥ 140 እና ከዚያ በታች የእናቶች ሞት ምጣኔ እንዲቀንስ ማድረግ፣ ከሚወለዱ ሕፃናት ከ1ሺህ ውስጥ 12 የሚሆነውን የአራስ ሞት መጠን መቀነስ፣ እናቶች በሰለጠነ የጤና ባለሙያዎች የሚወልዱበትን መጠን 95 በመቶ ማሳደግ መሆኑን ሪፖርቱ ያሳያል።

የጤና ሚኒስቴር ባለፉት 30 ዓመታት የእናቶች እና ጨቅላ ሕጻናት ምጣኔ ቅናሽ ማሳየቱን የሚገልጽ ጥናታዊ ሪፖርት በራሳቸው የትስስር ገጽ አስነብበዋል።

# "ከትላንቱ ጉዳት የነገ ተስፋችን ስለሚበልጥ ለቀጣይ ልማታችን ልንበረታ ይገባል"

-አቶ ከበደ አሰፋ

*የቀድሞ መቀሌ ከተማ መንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ኃላፊ*

**ሄርሞን ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- ትላንት ከደረሰብን ጉዳት ይልቅ የነገ ተስፋችን ስለሚበልጥ ሁላችንም ጉዳታችንን በመርሳት ለነገ ተስፋችን ትኩረት በተሻለ መልኩ ትግራይን ለመገንባት ልንበረታ ይገባል ሲሉ የሕግ ባለሙያና በቀድሞ ጊዜያዊ አስተዳደር የመቀሌ ከተማ መንገድና ትራንስፖርት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከበደ አሰፋ አመለከቱ።

አቶ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አሁን የሰላም ስምምነቱ ያጫረው ተስፋ ቀላል ኣይደለም፤ሰው የሚኖረው በተስፋ ስለሆነ የትላንቱን መጥፎ ጠባሳ በመርሳት ወደ ተሻለ ነገ መራመድ ያስፈልጋል። የትላንቱን መርሳት የሚቻለው ደግሞ ከነበረው ችግር ትምህርት በመውሰድ መሻገር እና ነገን በተሻለ ማስተካከል ሲቻል ነው።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በተለየ መልኩ ደግሞ ትግራይን ያጋጠመው ጉዳት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳት ስለሆነ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባም አስምረውበታል።

የወደሙ መሠረተ ልማቶች መልሶ ለመገንባት እና ሕዝቡ ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግም በመላው ሃገሪቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና በውጭ የሚገኙ የዲያስፖራ ማኅበረሰብን በማደራጀት ፎረም እንዲቋቋም ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ከበደ፤ ፎረሙ በተቀናጀ መልኩ በመምራት ትግራይ ወደ ነበረችበት ብቻ ሳይሆን በእጥፍ ለማልማት እና ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ ይሠራል ብለዋል።

እንደሚታወቀው እርስ በእርስ ለመፋለም የነበረን መጥፎ ታሪክ ወደ መልካም ሃሳብና አምራችነት በመለወጥ ለፀብ ከመተባበር ይልቅ ለልማትና ለበጎ አድራጎት መተባበር ለትግራይ ብሎም ለመላው ሀገሪቱ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን አሳስበዋል።

እንደ አቶ ከበደ ማብራሪያ ፤ በአሁኑ ወቅት ሁሉም ዜጋ ከኩርፊያ እና ከተበዳይነት ስሜት በመውጣት በሙሉ አቅም ወደ ለውጥ መግባትና በአዲስ ሃሳብ አዲስ ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። ይህ ማለት ግን ምንም እንኳ ጊዜው አሁን ባይሆንም ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ ግለሰቦች በሕግ አይጠየቁም ማለት አይደለም። ለአሁኑ ግን ቀዳሚው ጉዳይ ሰላምን የማረጋገጥና መሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት መልሶ የመገንባትና ሕዝቡን ማረጋጋት ነው።

በጦርነቱ ምክንያት በተለይ የትግራይ እናቶች ከፍተኛ ኃዘን ውስጥ መውደቃቸውን ያወሱት አቶ ከበደ፤ከደረሰባቸው የኃዘን ድባብ እንዲወጡ የማድረግ፣ ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት እና ከጦርነቱ የተረፉ ወጣቶች ተረጋግተው ወደ ትምህርት ገበታ እንዲገቡ የስነልቦና እገዛ እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

በመጨረሻም መላ ኢትዮጵያውያን ከመንግሥትና ሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም በሚቋቋመው ፎረም በመሰባሰብ ይህን መጥፎ አጋጣሚ ወደ መልካም ዕድል የምንቀይርበት ጊዜ አሁን ስለሆነ ተባብረን ሃገራችንን ከፍ ማድረግ ይጠበቅብናል ብለዋል።

# መንግሥት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

"የሰላም ስምምነቱ ለሕዝቡ እፎይታን ሰጥቶታል፤ አሁን እንደምናየው ሕዝቡ በደስታ ነው የተቀበለው" ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ አንዳንድ ቀዳዳዎች ሊኖሩ ቢችሉም ሰላምን ለማስፈን የሚደረገው እንቅስቃሴ በጣም ጥሩ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ዶክተር አረጋዊ አክለውም የመንግሥት ተቀዳሚ ሥራው በሕገ መንግሥቱ መሠረት ሕግ እንዲከበር፣ በሀገሪቱ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሰፍን ማድረግ ነው። ሃገር አፍራሽ እና ጽንፈኝነትን የሚያቀነቅኑ ኃይሎችንም እንዲቆጣጠር ሕገ መንግሥቱ ኃላፊነት ሰጥቶታል ብለዋል።

ዶክተር አረጋዊ እንደተናገሩት መንግሥት ሰላሙን ለማስቀጠል በሙሉ ኃይሉ ገብቶ ግዴታውን መወጣት አለበት። ከሰላም ማስፈን ሥራው በኋላም የአካባቢውን መሠረተ ልማት መልሶ መገንባት ፣ ጤና ተቋማት ሥራ እንዲጀምሩ ማድረግ ፣ትምህርት ቤቶች ወደሥራ እንዲመለሱ ማድረግ እና ኅብረተሰቡን ወደ ቀድሞ ኑሮው መመለስ ይጠበቅበታል።

የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የጦርነት ቀጠና ሆኖ ነው የኖረው ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ በአሁኑ ጦርነት ደግሞ የበለጠ ጉዳት ደርሶበታል ብለዋል። በዚህ ጦርነት የተጎዳው የትግራይ ክልል ብቻ ሳይሆን እንደሚታወቀው የአፋር እና የአማራ ክልልም በመሆኑ መንግሥት ከፍተኛ ሥራ ይጠብቀዋል ብለዋል።

ግጭቱ በሰላም መቋጨቱ ሕዝቡ ተረጋግቶ መኖር እንዲችል ያረገዋል ያሉት ዶ/ር አረጋዊ መንግሥትም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰላሙን ለመደገፍ እና ለውጡ ስር እየሰደደ እንዲሄድ አጥብቀው መሥራታቸውን እንዲቀጥሉ አሳስበዋል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት የደረሰውን ጉዳትና ዳግም የተጀመሩ መሠረተ ልማቶችን ለማየት መሄዳቸው ጥሩ ጅማሬ ነው፤ የበለጠም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉም አሳስበዋል።

አሁን መንግሥት ከሕወሓት ጋር ያደረገው የሰላም ስምምነት በውጪ ላሉ የሀገራችንን ሰላም ለማይፈልጉ ኃይሎች ችግራችንን በራሳችን መፍታት እንችላለን የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው ብለዋል ። ስለዚህ ሚዲያዎች ከውጪ አፍራሽ ኃይሎች ጋር በመሆን የሀገራችንን ሰላም የሚያደፈርሱ የውስጥ ባንዳዎችን ማጋለጥ ይኖርበታል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል ።

ዶክተር አረጋዊ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሰላም ከሌለ አብሮ መኖርና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ማከናወን ከባድ እንደሚሆን ተረድቶ ችግር ሲኖር በውይይት እየፈታ መቀጠል ይኖርበታል። የፖለቲካ ፓርቲዎችም የራሳቸው የሆነ ወጥ አቋም እና ጠንካራ ሀሳብ በመያዝ ሰላሙን መደገፍ አለባቸው። ሀገራችን ከድህነትና ከጦርነት መውጣት የምትችለው በሰላም መወያየት እና መደራደር ስንችል ነው።

# ብልጽግና ብቃት ያላቸው ተቋማትን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንዲሆኑም አሳስበዋል።

የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ የወጣቶች ሚና ከፍተኛ ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ብልጽግና ፓርቲ ባከናወነው አካታች ሥራ የወጣቶች ተሳትፎ በፓርቲው 51 በመቶ በላይ ደርሷል ብለዋል። ወጣቶች ወደ ፓርቲው መካተታቸው የወጣቶችን መብትና ጥቅም እንዲያስከብሩ ይረዳቸዋል ሲሉም አክለዋል።

የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የወጣቶች ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ሊጉን ለማጠናከር በትኩረት እንደሚሠራም ጠቁመዋል፡፡

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ሊቀመንበር ወጣት አስፋው ተክሌ በበኩሉ፤ ወጣቶች በለውጡ ሂደት በተመዘገቡ ሁለገብ ስኬቶች ውስጥ የማይተካ ሚና መጫወታቸውን አንስቷል።

ወጣቱ በአገባቡ ከተመራ እና ዕድል ከተሰጠው ለሀገሩ የማይሰስት እና በሀገሩ ጉዳይ የማይደራደር መሆኑን በተለያዩ መልኮች ማረጋገጡን በመጥቀስ፤ በአረንጓዴ አሻራ፣ በሌማት ትሩፋት፣ በስንዴ ልማት እና በሰሜኑ ክፍል የነበረውን ጦርነት በመመከት እንዲሁም በውጣ ውረድ የተሞላውን የዓባይ ግድብ ሥራ በማገባደድ ወጣቱ ታላላቅ አሻራዎቹን አኑሯል ብሏል።

ሀገራዊ ለውጡ እንዲመጣ ወጣቶች ብርቱ ተጋድሎ ማድረጋቸው የማይረሳ መሆኑን ጠቅሶም ከዚህም በተጨማሪ በአረንጓዴ አሻራ፣ በሌማት ትሩፋት እና በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች የማይተካ ሚና እየተወጡ መሆናቸውን ተናግሯል፡፡

እንደ ወጣት አስፋው ገለፃ፤ በአሁኑ ጊዜ ያለው ወጣት ሁለት አማራጮች አሉት፡፡ አንደኛው አማራጭ የተበላሹ እና የተዛነፉ ትርክቶችን ወደ መልካም ዕድል ቀይሮ መጠቀም ነው፡፡ ሌላኛው አማራጭ ደግሞ ሀገር ለማፍረስ ለሚተጉ፣ እኩይ ዓላማ ላላቸው ኃይሎች እጅ መስጠት ነው፡፡ ይህ ትውልድ የተጣሉበትን ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች የተወጣ በመሆኑ የመጀመሪያውንና አዋጩን አማራጭ በመጠቀም ወንድማማችነት እንዲሰፍንና አንድነት እንዲነግስ በርትቶ መሥራት ይጠበቅበታል ብሏል፡፡

# ባለፉት 10 ዓመታት ወደ ካዳስተር ሥርዓት የገባው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ይዞታ፣ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡

የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተር ኢንጂነር ጀማል ሐጂ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት፤ በከተማዋ ካሉት 424 ሺህ በላይ የመሬት ይዞታዎች መካከል በዘመናዊ የመሬት ይዞታ ምዝገባ ሥርዓት የተከናወነባቸው 110 ሺ ይዞታዎች ወይም አንድ አራተኛው ላይ ብቻ ነው፡፡

በወቅቱ የሰነድ ርክክብ አለማድረግ፣ በፊት የነበረው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ትክክለኛነቱ ባለመረጋገጡ እንዲሁም ሕገ-ወጥ ሰፈራዎች መበራከታቸው የዘመናዊ የመሬት ይዞታ ምዝገባው እንዲጓተት ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው ብለዋል።

በተጨማሪም በመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተሰጠባቸው ቦታዎች መኖራቸውና ባለ ይዞታዎች ለዘመናዊ የመሬት ይዞታ ምዝገባ ሥርዓቱ የሚሰጡት ግምት አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም የዘመናዊ መሬት ምዝገባ



ፎቶ - በገበበ ገብሬ

ኢንጂነር ጀማል ሐጂ

ቴክኖሎጂው አለመስፋፋት ምዝገባው እንዳይፋጠን እንክን ሆኗል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ኢንጂነር ጀማል ገለጻ፤ አሁን ያለው የይዞታ ምዝገባ ቴክኖሎጂ የሊዝና መሬትና፣የእቅድ መረጃዎችን ከመያዝ አንጻር ውስንነቶች አሉበት። አሠራሩን ለማፋጠን እንዲረዳ ባለፉት ሁለት ወራት ቴክኖሎጂው ላይ ማሻሻያ ለማድረግ ወይም ሙሉ በሙሉ ለመቀየር የሚረዳ ውይይት ከባለድርሻ አካላት ጋር ሲከናወን ቆይቷል።

ከቴክኖሎጂው ማሻሻያ ባለፈ በመዲናዋ ትክክለኛነታቸው ያልተረጋገጡ የመሬት ባለይዞታነት ሰነዶች በርካታ ናቸው ያሉት ኢንጂነር ጀማል ፤ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ 29 ሺ ይዞታዎች የሕጋዊነት ጥያቄ እንዳለባቸው መረጋገጡን ገልጸዋል፡፡

የሕጋዊነት ጥያቄና ክርክር ያለባቸውንና የቀድሞ ፋይሎች የማጣራት ሥራ ሲከናወን መቆየቱን ገልጸው፤ ከመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ የመሬት ይዞታ ምዝገባዎች እየተከናወኑ መሆኑን ምክትል ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል የይዞታ ምዝገባ ሥርዓቱን ቀልጣፋ ለማድረግ ከአሁን በፊት ውስብስብ የነበረው አሠራር ተቀይሷል። በአሠራሩ መሠረት የምዝገባ ማረጋገጫውን በአንድ ክፍለ ከተማ ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ሌላኛው ክፍለ ከተማ የምሄድበትንና ሥራዎችን የምንጀምርበት አሠራር ተግባራዊ ተደርጓል ሲሉ አስታውቀዋል።

ከ10 ዓመታት በፊት የዘመናዊ የመሬት ይዞታ ሥርዓቱ ወደ ሥራ ሲገባ በፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት እንዲመራና ሥራውን በሁለት ዓመት ውስጥ እንዲያጠናቅቅ ታቅዶ ነበር። ሆኖም ሥራው በታቀደለት ጊዜ ባለማጠናቀቁ ከለውጡ በኋላ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ቋሚ መሥሪያ ቤት ሆኖ እንዲቋቋም ተደርጓል ብለዋል።

ይሁንና ተቋሙ ቀድሞ ወደ ነበረበት የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤትነት እንዲቀየርና ተቋማዊ አደረጃጀት ተፈጥሮለት በተሻለ መንገድ በ2015 ዓ.ም ወደ ሥራ እንዲገባ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በመጨረሻም የመሬት ይዞታ ምዝገባው በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቅ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተለይም የፕላን ሚኒስቴር፣የመሬት ልማት አስተዳደር ተቋማት እንዲሁም የመሬት ባለይዞታዎች የተቀናጀ ሥራ እንዲያከናውኑ ኢንጂነር ጀማል ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስሰላማችን የሚገባውን ጥበቃና ክብር እንስጥ!

ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያመለክቱት የአንድ አገር ሰላም ባለቤት የዚያች አገር ሕዝብ ነው። ከዚያ ሕዝብ ውጪ የሰላሙ ባለቤት ሊሆን የሚችል ማንም የለም፤ ይኖራል ብሎ ማሰብም የዋህነት፤ ከዚያም ባለፈ ስለ የዋህነት የሚከፈልን ዋጋ ማብዛት ነው።

ስለ ሰላም ተምሳሌት የሆኑ ማኅበረሰቦችም ሆኑ ሕዝቦች ተጠቃሽ ስለሆኑበት ሰላማቸው ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሰሩ፤ በየዘመኑ የነበሩ የሰላም እሴቶቻቸውን ዘመኑ ከደረሰበት አስተሳሰብ ጋር እያዋሀዱ እና አቅም እየገነቡ የሄዱ ናቸው።

ከዚህም ባለፈ በትውልዶች ላይ ወጥና ቀጣይነት ያለው የሰላም እሴቶች ግንባታ በማከናወን፤ ትውልዶች ለራሳቸው ነገዎች ከሁሉም በላይ ስለ ሰላም አበክረው እንዲሰሩ፤ ይህንንም የእለት ተእለት ተጨባጭ ተግባራቸው በማድረግ ጭምር ነው።

በተቃራኒም በአብዛኛው በሰላም እጦት የዓለም ሕዝብ መነጋጋሪያ የሆኑ አገራት፤ እዚህ ሁኔታ ውስጥ የገቡት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሰላምን ዋጋ አቅለው በማየታቸው ነው።

"የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ" እንደሚባለው፤ ቀደም ባለው ጊዜ በብዙ አልባሌ ስብከቶች ትርጉሙና ዋጋው የቀለለባቸውን አገራዊ ሰላማቸውን መልሰው ለማምጣት እየሄዱበት ያለው መንገድ ከነሱ እጅ ወጥቶ፤ በሌሎች የሰላም ነጋዴዎች እጅ ገብቶ የፖለቲካ መቆመሪያ ካርድ ሆኗል። ለዚህም እየከፈሉት ያለው ዋጋ የቅዠት ያህል ሆኖባቸዋል።

ለዚህም የአሁኖቹን ሶሪያን፣ ኢራቅን፣ ሊቢያን እና የመንን ማየት በቂ ነው። ብሄራዊ ጥቅምን፣ ሰላምንና አንድነት ማእከል ያላደረገ የትኛውም አይነት የለውጥ መንፈስና መነቃቃት መጨረሻው ጥፋት እንደሆነ አመላካች ነው።

ከዚህም ባለፈ የትኛውም አይነት የለውጥ መነቃቃት ለለውጡ ስኬት ዋነኛ አቅም የሚሆነውን አገራዊ ሰላም ታሳቢ ካላደረገ ፣ ለውጡ ተስፋ ከሚያደርገው አገራዊ አጀንዳዎች ይልቅ የሰላም እጦቱ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ወደኋላ መላሽ እንደሚሆን በተጨባጭ ያሳየ ነው።

በእኛም አገር ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የተስተዋለው ከዚህ በብዙ የተለየ አይደለም። በለውጥ መንፈስ የተነቃቃውና የለውጡ ዋነኛ ኃይል ሆኖ የተገለጠው ሕዝባችን፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በእጁ የነበረውን ሰላም በቁርጠኝነት መጠበቅ ባለመቻሉ ላልተገቡ ችግሮች ተዳርጓል።

በተራ አሉባልታዎች እና ለውጡን ለማደናቀፍ ስራዬ ተብለው በተፈበረኩ ጸረ-ሰላም ትርክቶች እና ሴራዎች ሕዝቡ ሰለባ በመሆኑ የራሱን ውስጣዊ ሰላም ጨምሮ ማህበረሰባዊና አገራዊ ሰላሙ አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል።

አገር አስገዳጅ በሆነ ጦርነት ውስጥ ከፍ ያለ ዋጋ እየከፈለችበት በነበረችባቸው ወቅቶች ሳይቀር፤ አንዳንዶች አገር ወድቃበት የነበረውን የህልውና ስጋት፤ ከአሸናፊና ተሸናፊነት ትርክት ወጥቶ ማየት የሚያስችላቸውን እይታ አጥተው ተስተውለዋል።

ዛሬም ቢሆን የሰላምን ሁለንተናዊ አገራዊ ዋጋ ማስተዋል ያልቻሉ አንዳንድ ኃይሎች በፌደራል መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰበትን ስምምነት ከማቅለል ጀምሮ ትርጉም አልባ ለማድረግ፤ ከዚህ ይልቅ ወደ ቀደመው የፖለቲካ ባህላችን የአሸናፊ፤ ተሸናፊ ትርክት እንድንመለስ ለመምከር ሲዳዳቸው ይታያል።

የእነዚህ ኃይሎች ተልእኮ ምንም ይሁም ምን፤ ሕዝባችን ከቀደሙት የሽግግር ታሪኮቻችንም ሆነ ትናንት ብዙ ዋጋ ካስከፈለን የጦርነት ውሎአችን በመነሳት በእጃችን ላለው ሰላም የሚገባውን ጥበቃና ክብር በመስጠት መክፈል የሚገባንን ዋጋ መክፈል ግድ መሆኑን በአግባቡ ሊረዳ ይገባል።

አሁን የሚያስፈልገን በብዙ ዋጋ ተመልሶ በእጃችን እየገባ ያለውን ሰላም እንዴት ሙሉ በሙሉ ማጽናትና በእጃችን ማስገባት እንችላለን? ወደፊትስ ለብልጽግናችን መሰረት የሆነው ሰላማችን ከእጃችን እንዳይወጣ ምን ማድረግ አለብን ለሚሉት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት ነው።

ይህን ማድረግ ባለመቻላችን ምክንያት አገራዊ ሰላማችን በሰላም ነጋዴዎች፤ እና በሰላም የፖለቲካ ቆማሪዎች እጅ ከገባ እንደ አገር አንድ ሆነን የመቆማችን ጉዳይ በራሱ ጥያቄ ሊሆን የሚችል ነው። ስለሆነም በራሳችን ፍላጎትና አቅም የተገኘውን ሰላም ለማጽናት ሁሉም በኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀስ ይገባል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ከእኔ... እኔ...እኔ...ወጥተን የጠፋብንን እኛን እንፈልግ !

ብስለት

እውነት አፋችን ላይ ሰላም የሚለው ቃል እንደሚቀለን፤ በወሬ ሰላምን እንደምንናፍቅ ለሰላም ተግባራዊነት እንነሳለን ወይ ? ብዬ ልጠይቅ ወደድኩ። እስኪ አንድ እንበል በታሪክ እንጣላለን በጣም የሚገርመው ታሪክ ሲሰራ ለአገር ድልና የበላይነት ከፍ ለማድረግ ሆኖ ሳለ ለአገር ታሪክ የሰሩ ድንቅ አባቶቻችንን በብሄር ደሴት ውስጥ ከበን ለማሰር እንሞክራለን።

የአገርን ሉአላዊነት ያስጠበቁትን አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውን አፍስሰው ከሰው በላይ ቀና እንድንል ዋጋ የከፈሉልንን ታሪክ ሰሪዎቻችንን የኔ፤ የኔ በሚል ውሃ በማይቋጥር ሀሳብ፤ የተከበረ ክብራቸውን ስናቀል፣ ባልተወለድንበት ዘመን በተሰራ ታሪክ ስንደነቋቆል እውነት እኛ ሰላምን እንፈልጋለን ያሰኝም ትላለችሁ።

ሁሉም በዘመኑ የዘመኑ ጀግና መሆን ሲገባው፤ ዘመን የሚጠይቀውን ገድል እንደማስቀመጥ ይልቁኑ በጠባብነት ገመድ ተተብቶብ ሲደነቃቀፍ ከመመልከት የበለጠ ምን ፀያፍ ድርጊት ይኖር ይሆን ?

ልቀጥል፤ በዘር እንጣላለን። ወደን መርጠን ባልተወለድንበት፤ እገሌ ከዚህኛ እገሊት ደግሞ ከዛኛው እየተባለ ጎጣጎጥ ስናበጅ ምንም አይነት የራስ አስተዋፅኦ በሌለበት በፈጣሪ ፍቃድ በሆነ ማንነት ለሞት ለመጠላላት እራሳችንን አሳልፈን ሰጥተናል።

ሰው ሰውነቱ ቀርቶ አማራ፥ ኦሮሞ፥ ትግሬነቱ ሲጎላ ከዚህ የባሰ ሰላምን የሚየሳጣ፣ ሰላምን የሚያደፈርስ ይኖር ይሆን ? እናስ ዘር ቆጠራችንን ሳናቆም ስለምን ሰላምን ናፈቅናት? ሰላም በናፍቆት ሰላም በማውራት የሚገኝ ቢሆንማ ጉንጫችንን ስናለፋ በዋልን ነበር።

በኃይማኖት እንጣላለን፤ እዚህ ጋ ደግሞ ሌላ ትኩሳት አለ ዘፉኙ። መቼስ ሰላም ናፋቂዎቹ መካከል ፈጣሪን ከሚያምኑት የላቀ ማንም አይገኝም። ማንም ሰው ማንነቱ ተከብሮ ይኖርለት ዘንድ የሌሎችን ኃይማኖት ማክበር ግድ ሊለው ሲገባ ባልተገራ አንደበት አንዱን ሀይማኖት የበላይ ሌላውን የበታች እያደረጉ ማንኳሰስ ማጣጣል፤ ባልተገባ ቋንቋ የሌላውን ሐይማኖት በስርአት አልበኝነት መዘርጠጥ እውን ከሰላም ፈላጊዎች የሚገኝ ነው ብላችሁ

**ሰላም በእውነት የሚፈልግ የሚበረበርና የሚሰመድ ነው። ሰላም ሰላም ብቻ ማለት ሰላምን አያመጣም ካለን ክፉ አመል ቀንስ አድርገን ለደግ ደጉ ጊዜ ስንሰጥ ነው እውን የሚሆነው**

ታምናላችሁ ?

በቋንቋ እንጣላለን ፤ አንድ ቋንቋ የአንድ ህዝብ ወይም የብሔር ቋንቋ ወይም ከተለያዩ ህዝቦች እና ብሄሮች የሚግባቡበት ነው። የቋንቋ የግንኙነት ስርዓት ሲሆን ይህም በአፍም በፅሁፍም ሊሆን የሚችል ነው። ዋና አላማው በሰዎች መካከል መግባባት እንዲኖር በሚያረጋግጡ የድምጽ፣ የምልክት፣ የሰዋሰዋዊ ህጎች ድምር ነው። ታዲያ ይህ ለመግባቢያነት የተፈጠረ መሳሪያ ጭራሽ መጣያና መነጣጠያ ሲሆን ምን ይሉያል!።

በቋንቋ ተግባብቶ ዓለም ከምድር አልፎ ሰማይ ላይ በሚወጣበት ዘመን፤ ጨረቃና ፕላኔቶችን በሚያጠናበት በዚህ በዘመነ ዘመናዊነት የእገሌ የእገሊት ዘር እንዲህ አለ እንዲህ አለች በሚል ጥብብ ያለ እንደ ጋሪ ፈረስ ብቻ ፊት ፊቱን እያየን የዓለምን ስፋት ሳንመለከት አንድ አይነት ቋንቋ እየተነጋገርን ቋንቋችን ተደበላልቆ ያን ማረቅ የተሳነን እኛ እውን ሰላምን አፋችን ላይ እንዳለው ከልብ እንፈልገዋለን?

ሌላ ልጨምር፤ በፖለቲካ አመለካከት እንጣላለን፣ ምንም ሰው የሌላውን አመለካከት ለመጨፍለቅ እስካልሞከረ ድረስ የራሱ የሆነ ፖለቲካዊ አመለካከት ሊኖረው መብቱ ነው። ግን እኔን ስሙኝ፤ እኔን ተከተሉኝ በሚሉ አዋቂ ነን ባዮች የተነሳ የራስ አመለካከት የወል ይሆንና የፀብ መነሻ ይሆናል። በግድ እምነትና አመለካከትን ለመጫን በሚፈጠር ሽኩቻ ውስጥ ነው ፖለቲካ ራሱ ዱላ መማዘዣ፤ ነፍስ መጣፊያ የሚሆነው።

ጥንታዊት፤ ለዓለም የአንድነት ተምሳሌት የሆነችው አገራችን፤ የቀደሙት አባቶቻችን በብዙ የተጋድሎ መስዋእትነት ያቆዩልን አገራችን ባንዲራ /አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ/ መጣያችን መሆኑስ ምን ይሉታል? አንድ ሰላም ረሃቤ ነው ከሚል ማህበረሰብ የአገር መለያ የሆነው ቀለም ሲታይ ፍቅርን እና አንድነትን መስበክ ሲኖርበት መለያያ የሚሆንበት ምክንያትስ ምድነው? ።

ይህ ፀብ ያለሽ በዳቦ የሆነው አመላችንን በጉያችን ሸሽገን አገራችንን ሰላም ያድርግልን ቅብርጥሶ ስንል አያምርብንም ሰላም በአፍ ሳይሆን በተግባር የሚገለጥ ነው። ሰላም ሰው የመግደልን ያህል አሰቃቂ ባይሆንም፤ በይቅርታ ራስን መስበርን ዝቅ ማለትን፤ ለእያንዳንዱ ነገር ልብን ክፍት ማድረግ በቅንነት ማሰብን፤ ራስን በትህትና መግደልን ይጠይቃል።

ሰላም በእውነት የሚፈልግ የሚበረበርና የሚለመድ ነው። ሰላም ሰላም ብቻ ማለት ሰላምን አያመጣም ካለን ክፉ አመል ቀንስ አድርገን ለደግ ደጉ ጊዜ ስንሰጥ ነው እውን የሚሆነው።

እስኪ አስቡት በስንቱ እንጣላለን፣ እንሰዳደባለን፣ ሰውን እናንቋሽሻለን፣ እንገዳደላለን። ይበቃል.... በቃ። ቆም ብለን ማሰቢያ ጊዜያችን አሁን ነው። እኔ የወደድኩትን ውደዱ፣ እኔ ያመንኩትን እመኑ፣ እኔ የጠላሁትን ጥሉ፣ እኔ ያልኩትን በሉ በቃ! እኔ፤ እኔ፤ እኔ ይብቃ እና የጠፋብንን፤ አንድ የሚያደርገንን፤ የሚያቀራርበንን እኛን እንፈልግ።


እውነተኛ እኛነታችን ሰላምን ስለመሻቱ፤ ባህሪያችን ሰላምን ስለመፈለጉ እናረጋግጥ፤ ራሳችንን እንመርምር። ውስጣችንን አሳምነን በእውነት መሻት ሰላምን እንፈልገው። ለይምሰል ለታይታ አፋችን ላይ ብቻ ሰላም ሰላም አንበል። ውስጣችን ሰላም ከሌለ ሰላም ከየት ነው የሚመጣው? በሰላም መኖር ከልብ ከፈለግን ከልባችን እንጣር። ልብ ያለው ልብ ይበል !

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ፋሽንና ቀለማት

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



የሰው ልጅ የመኖሩን ትርጉም የሚገልጥበት ልዩ ጥበብን የታደለ ፍጡር ነው። በዚህ ጥበብ ደስታውን ያገኛል። ከእነዚህ መሃል ደግሞ የፋሽን አልባሳት ዲዛይንና ቀለማት አንዱ ነው። ለመሆኑ የፋሽን አልባሳትና ቀለማት ትስስር በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ በምን መልኩ ይገለፅ ይሆን?

ፋሽንን ከውበት፣ ውበትን ከዘመን፣ ዘመንን ከጥበብ ስናዋህድ በነዚህ ሁሉ መሃከል ቀለማት የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ። ፈጣሪ ታላቁን የሰውን ልጅ ከአፈርና ውሃ ካበጀ በኋላ ሰው እንዲሆን ያደረገበት ጥበብ እስትንፋስ ነው። ወደ ፋሽን ጥበብ ስንመጣም የፋሽን ጥበበኛ እጆች ጨርቁን ከዲዛይኑ አጣምረው ከሰሩት በኋላ ፋሽኑን በቀለማት ነብስ ካልዘሩበት፣ ፈጠራቸው ሰውነትን ከመሸፈንና ብርድን ከመከላከል በዘለለ በዘመንና ፋሽን የውበት ማህደር ውስጥ ዋጋ አይኖራቸውም። ይህ ማለት ጣፋጭ ኬክ አዘጋጅተን ክሬሙን ሸሮ ወጥ እንደማድረግ ነው። በፋሽን ዲዛይን ውስጥ ውበትን ለመፍጠር የቀለማትን ሚስጥርና ትክክለኛ ቦታ ለይተን ማወቅ አለብን።

በዘመናዊ ፋሽን ውስጥ ቀዳሚው ነገር እይታን መሳብ ነው። በመጀመሪያ እናያለን፣ ያየነውንም እንወዳለን፣ የወደድነውንም ምርጫችን እናደርገዋለን። ገና በመጀመሪያው እይታ ቀለማት ምርጫችንን እንድንወስን የማድረግ አቅም አላቸው። በእርግጥ ውበት እንደምርጫ ነው። አንዱ የወደደውን ሌላኛው ሊጠላው፣ ያደነቀውንም ሊያንቋሽሸው ይችላል። ውበትና ፋሽን እንደምርጫችን ቢሆንም፣ በምርጫችን ውስጥ አስገዳጅ የሆኑ መመዘኛዎች አሉ። እነዚህም ባህል፣ ወግ ልማድ፣ ሀይማኖትና ያደግንበት ማህበረሰብ ናቸው።

ቀለማት ከስነ ውበትና ከግለሰባዊ ምርጫ ሰፋ ባለ መልኩ በባህልና እምነት እንዲሁም አገራት ውስጥ ልዩ ቦታና ትኩረት ይሰጠዋል። በሳይንሱ የሚታወቁት ቀለማትን አገራት ከራሳቸው ባህላዊና ስነልቦናዊ ሁኔታ በመነሳት የሚሰጡት ትርጓሜ አላቸው። በአብዛኛው ማለት በሚቻል መልኩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀለማት የሚከተለውን ትርጓሜ እንደአግባብነቱ እንዲይዙ ተደርገዋል። በዚህ መሰረትም ጥቂቶቹን ብንመለከት፤

ቀይ ቀለም:- ጥልቅ ስሜት፣ ፍቅር፣ ቁጣ… ብርቱካናማ:- ጉልበት፣ ደስታ፣ ህይወት… ቢጫ:- ደስታ፣ ተስፋ፣ ማታለል… አረንጓዴ:- አዲስ ጅማሮ፣ የተትረፈረፈ፣ ተፈጥሮ… ሰማያዊ:- ረጋ ያለ፣ ኃላፊነት፣ ሀዘን… ሐምራዊ:- ፈጠራ፣ ንጉሳዊ፣ ሀብት… ጥቁር:- ምስጢር፣ ውበት፣ ክፋት… ግራጫ:- ተለዋዋጭ ስሜት፣ ወግ አጥባቂ፣ መደበኛነት… ነጭ:- ጥሩነት፣ ንጽህና፣ በጎነት… ቡናማ:- ተፈጥሮ፣ ጤናማነት፣ ጥገኛነት…የሚሉ ትርጓሜዎችን ይይዛሉ። የተዋጣለት የፋሽን ዲዛይን ለመስራት ስናስብም አስቀድመን፣ ስራችንን የምናቀርብለት ማህበረሰብ በየትኛው የትርጓሜ መደብ ውስጥ እንዳለ ማጤን አለብን።

ፋሽን እንደ ዘመኑና እንደ ሁኔታው ሊቀያየር ይችላል። በፋሽን ውስጥ ያሉት ቀለማት ግን ሁልጊዜ ከሰው ልጆች ስብዕናና ማንነት ጋር ተያያዥነት አላቸው። ድምጽ አልባ መሳሪያ እንደመሆናቸውም ቃላት የማይገልጹትን እልፍ ትርጓሜዎች ይዘው ይገኛሉ። በአገራችን ታሪክ ውስጥም በኃይማኖታዊም ሆነ ባህላዊ እሴቶች ውስጥ ቀለማት ሚስጢራዊ ይዘት እንዳላቸው እንመለከታለን። በደስታ ጊዜ የብሩህነት መገለጫ የሆነውን ነጭና በተለያየ ቀለማት ያሸበረቀውን ጥለት፣ እንዲሁም ጎላ ብለው የሚታዩ የቢጫ፣ ቀይና አረንጓዴ አልባሳት ይዘወተራል።

በሃዘን ጊዜያት ደግሞ ደብዘዝ ብለው የሚታዩ ልብሶችን በተለይ ጥቁር ቀለም እንጠቀማለን። ታዲያ አንድ አባቱ ወይም እናቱ የሞተበት ሰው ከቀብር መልስ እቤቱ ገብቶ ነጭ በነጭ ለብሶ ቢወጣ ማህበረሰቡ የሚረዳው ይህ ሰው በአባቱ ወይም በእናቱ ሞት ደስተኛ መሆኑን ነው። ባህልና ስርዓትን ከመጣሱ በተጨማሪ እንደ ጨካኝና አረመኔ አሊያም እንደ እብድ ሊቆጠር ይችላል። ይሄም ቀለማት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ምን ያህል ዋጋ እንዳላቸው ያሳየናል።

በኃይማኖት ውስጥ ያለው የቀለም እይታና ትርጓሜ ደግሞ ከባህል የጠነከረ ነው። እያንዳንዱ የቀለም ጠብታ ልዩ ሚስጥራትን የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። የምንጠቀማቸው ቀለማት እራሳቸውን ችለው እንደ ፊደላት የሚነበቡ ናቸውና፣ ቀለማቱን በተገቢው ካላሰባጠርናቸው ፊደላቱ የተዘበራረቀ መጽሃፍ ጽፎ እንደማሳተም ይሆንብናል። በተመሳሳይ በፋሽኖች ውስጥም ጊዜና ሁኔታን ያላገናዘበ ቀለማትን የምንጠቀም ከሆነ የምናቀርብለት ማህበረሰብ ይህንን የመቀበል ፍላጎት አይኖረውም። ጊዜና ሁኔታዎችን ማገናዘብ በእጅጉ ወሳኝነት አላቸው። በአብዛኛው የምንከተላቸው የፋሽን ፈጠራዎች ውድቀት የሚጀምረው ከእነዚህ አንጻር ነው። የፈጠራዎቹ እድሜም በጣም አጭርና እንደ መብረቅ ብልጭታ ገና ሳይታዩ የሚከስሙ ይሆናሉ።

ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶች፣ የጥበብ ሰዎች እንዲሁም በርካታ የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ባለሙያዎች ስለ ቀለማት አፈጣጠርና ስብጥር በተለያዩ ጊዜያት ጥናትና ምርምር አካሂደዋል። ሁሉም የራሳቸውን መላምት ከመሰንዘር ውጭ ይሄ ነው የሚባል የቀለማትን ስነ ልቦናዊ ቀመር የደረሰበት ግን የለም። በአለማችን በቁጥር ከ10 ሚሊዮን በላይ ቀለማት እንዳሉ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን እያንዳንዳቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላሉ። ለዚህም ነው የፋሽን ዲዛይነሮች አልባሳትን ዲዛይን በሚያደርጉበት ወቅት ከውበት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከስነ ልቦና ውቅርና ተፅዕኖ አንፃር የሚቃኙት። በኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ደግሞ ደማቅ ቀለማት ይፈራሉ። ደብዘዝ ያሉ ቀለማት ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ለበዓላትና ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች ካልሆነ በቀር ደማቅ ቀለማት ያስፈሩናል። ምቾት አይሰጡንም። አሁን አሁን ግን በከተሞች አካባቢ በተነሳው የፋሽን አቢዮት ቀለማትን ደፍሮ የመጠቀምና በእነርሱ በተቃኙ አልባሳት የመዋብ ልምዱ ቀስ በቀስ እየዳበረ በመምጣቱ የባህል አብዮቱን እየቀሰቀሱት ነው።

ፋሽንና ቀለማት ነጠላ ፍቺ ሰጥተን እንደዚህ ናቸው ለማለት የማያስደፍሩ ጥልቅ የሆነ ይዘትና ሀሳብ ያላቸው አውደ ብዙ ቃላት ናቸው። በዚህ ጹሁፍ ውስጥ በብዛት ከአልባሳት አንጻር ቢገለጹም ቅሉ ተቀዝፈው የማያልቁ ውቅያኖስ፣ ተገልጠው የማያልቁ መጽሐፍት ናቸው። እኛም ጀመርነው እንጂ አልጨረስነውም።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ሲስተሙ እና መመሪያው

**አቤል ገ/ኪዳን**

ባለፈው ሰሞን ለአንድ ጉዳይ በአቅራቢያዬ የሚገኝ ወረዳ ሄጄ ነበር። እንደተለመደው የወረዳው ግቢ በትርምስ ተሞልቶ ማን ለምን ጉዳይ አንደመጣ በማይታወቅበት መልኩ የቅዳሜ ገበያ መስሏል። እኔ የሄድኩት ደግሞ ወሳኝ ኩነት የሚባለው ከገበያም በላይ የሚደምቅ ቦታ ነው። በጊዜ የደረስኩ ቢመስለኝም ሰልፉ ግን ተጠማዞ የትና የት ሄዷል። እንደማንኛውም ሰው ተሰለፍኩ። ሰራተኞቹ አሰራራቸው ዲጂታላይዝድ ነው ቢባልም መንቀራፈፋቸው ግን ጥልፍ እንደሚሰራ ሰው ነው። አስተሳሰብ ዲጂታላይዝ ካልሆነ ስርአት ዲጂታላይዝ ቢሆን ጥቅም እንደሌለው ሁነኛ ማሳያ ይሆናሉ።

ከብዙ መቆየት በኋላ ደረሰኝ። መሳሪያ ተደግፎበት የሚሰራ የሚመስል አንድ ስልቹ ሰው ቆጣ ቆጣ እያለ ወደ መዝገብ ቤት መራኝ። መዝገብ ቤት ያለችው ደልዳላ ሴትዮ ከሰውየው በበለጠ በስራውም ብቻ ሳይሆን በህይወቷም የተበሳጨት ትመስላለች። ማነው የላከህ አለችኝ። ወደላከኝ ሰውዬ ጠቆምኳት። እኔ የማንንም ፋይል በመጎተት ክንዴ ተገነጠለ፤ ለምን እነሱ ኮምፒተር ላይ አያዩላችሁም ብላ ተፈናጥራ ተነሳች። ፋይሉን ካለበት ጎትታ አምጥታ አገላብጣ ማየት ጀመረች። እርግጥ የኛም ቤት ፋይል ከመወፈርም በላይ በጣም አርጅቶ ለአይንም ይከብዳል። የሆነ ነገር ጽፋ ወረቀቱን ሰጠችኝ፤ ወደ ሰውየው ተመለስኩ። ወረቀቱን አየና በል ወደ ወረፋህ ተመለስና ተራህን ጠብቀህ ትስተናገዳለህ አለኝ። ተመልሼ ተቀመጥኩ።

ተራዬ ሲደርስ ኮምፒውተር ላይ ወደተቀመጠ ወጣት ልጅ ሄድኩ። ለምን ቀስ ብለው እንደሚሰሩ አሁን ገባኝ። ልጁና ሲስተሙ ብዙም አይተዋወቁም። ስለዚህም ቀስ እያለ ነው የሚሰራው። የሲስተሙን አንዳንድ ክፍል እንደማይረዳው ከአሰራሩ ማየት ችያለሁ። መረጃዎችን እየጠየቀኝ ሞላ። ከዚያ ግን መሞላት ግዴታ ያልሆነበት ክፍል ላይ ደረሰ። መረጃ ሲጠይቀኝ ይህ ክፍል ግዴታ እንዳልሆነ ነገርኩት። ግዴታ ነው አለኝ። ግዴታ እንዳልሆነ ኮምፒውተሩ ላይ እንደሚያሳይ ባመላከተውም ሊሰማኝ ፈቃደኛ አልሆነም። ሞላው። መረጃው ተጠናቆ ሲወጣ እኔ ከምፈልገው በተቃራኒው ሆነ። ሁሉንም በተራ አናገርኳቸው። አንዳቸውም ስህተታቸውን ለማመን አልፈለጉም። ሲስተሙ ግድ ይለናል አሉ። ሲስተሙ የግድ እንደማይል ባሳያቸውም ሊቀበሉ አልፈቀዱም። ሸንፈት መሰላቸው። በኋላ አናግረው ተብዬ ወደ ቡድን መሪው ጋር ደረስኩ። ወጣት ነው። ጉዳዬን ከሰማኝ በኋላ ትንሽ እንድጠብቅ ነግሮኝ ሄደና ሌላ ጉዳይ ፈጽሞ ሲመጣ አወራን። መመሪያው ይፈቅዳል አለ። ሌሎቹ አይፈቅድም አሉ። እርስ በርስ ክርክር ተጀመረ። ክፍለ ከተማ እና ሌላ ወረዳ ደወሉ። በመጨረሻ መመሪያው እንደሚፈቅድ ተረጋገጠና በድጋሚ ተስተካክሎ ተሰራልኝ።

ከአንድ ቢሮ ጠቅላላ ሰራተኛ መመሪያ በትክክል የሚያውቀው አንድ ሰው ብቻ መሆኑ አስገረመኝ። ብዙዎቹ መመሪያውን አያውቁትም ወይም የሚያውቁት በአንድ ወቅት የነበረውን ብቻ ነው። ሲለወጥ አልሰሙም ወይም አላስተዋሉም። ይሄ አንደኛው ችግር ነው። መመሪያ ተለዋዋጭ ነው። ያን ግን የሚረዳው ሰው ጥቂት ነው። ብዙው ሰው እንደ መንፈሳዊ ህግ አንዴ ከሰፈረ የሚቀየር አይመስለውም።

ዋነኛው ችግር ግን የመመሪያ እውቀት አለመኖር አይደለም። ስንፍና ነው። እንዳስተዋልኩት ብዙዎቹ አለማወቃቸውን ወይም ስህተታቸውን የሚሸፍኑት መመሪያው አይፈቅድም ወይም ሲስተሙ አይፈቅድም በሚል ሽፋን ነው። የትኛው መመሪያ መቼ የወጣው መመሪያ ቁጥር ስንት ቢባሉ ማስረዳት አይችሉም። እንዲሁ በደፈናው መመሪያው ይሉሃል። ህዝብም መንግስት ያወጣው መመሪያ ከሆነ መቼስ ምን አደርጋለሁ ብሎ እሺ ይላል። በዚህ የተነሳ መንግስት ባላወጣው መመሪያ ህዝብ ይጉላላል። ብዙው ህዝባችን በተለይ እናቶችን እና አባቶች ዛሬም ቢሆን መንግስትን የሚያምኑ ናቸው። የመንግስት መመሪያ ነው ከተባሉ እሺ ብለው ነው የሚሄዱት። በዚህም የተነሳ ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት ሳያገኙ ነው የሚሄዱት ማለት ነው። ይህ መንግስት ገቢ፤ ህዝብን አገልግሎት ያሳጣል። ምሬትን ይወልዳል። ምሬት ደግሞ ሲጠራቀም አመጽን ይወልዳል። እንዲህ አይነቱ አመጽን የሚፈጥሩት እንዝላል ሰራተኞች ይሆናሉ ማለት ነው።

ሲስተምም ላይ እንደዚያው። በጣም ያስገረመኝ ራሱ የጻፈው ጽሁፍ ላይ ያለን የፊደል ግድፈት ሲስተሙ ነው ሲለኝ ነው። ሲስተሙ በባለሙያዎች የተዘጋጀ ነው። ምን ተብሎ እንደሚጻፍ በግልጽ ተቀምጧል። status የሚልን ቃል states ብሎ ሲጽፍ ስህተት እንደሆነ ብነግረው ሲስተም ነው ብሎኝ ድርቅ አለ። በሁለቱ ቃላት መሀከል ያለው የፍቺ ልዩነት በጣም ሰፊ ነው። ይህ ዶክመንት በዓለም ዙሪያ የሚሰራ ዶክመንት ነው። ስለዚህ ይህ ዶክመንት የኢትዮጵያን መንግስት አቅም የሚያሳይ ነው። ታዲያ 120 ሚሊየን ህዝብ የሚመራ መንግስት እንዲህ አይነት ስህተት ተሳሳተ ቢባል ማን ያምናል። መንግስት ተሳስቶ አይደለም፤ ሲስተሙ አስገድዶም አይደለም፤ ሲስተሙ ላይ ያለው ሰው ንዝላልነት ግን ይህን አላስፈላጊ ስህተት ፈጥሯል።

በጥቅሉ ብዙዎች መመሪያ እና ሲስተምን እነሱ ላለባቸው ንዝላልነት፤ የቀናነት ችግር እና የሙስና ዝንባሌ እንደመጠቀሚያ እያደረጉት ነው። ይሄ በእርግጥ የእነሱ ችግር ብቻ ሳይሆን የብዙ ህዝባችን ችግር ነው። እሱ የማያውቀውን እውቀት እንደ እውቀት የማይቆጥር፤ እሱ ያልሰማውን መረጃ እንደ ፈጠራ ወሬ የሚያናንቅ፤ ለአዲስ ነገር ክፍት ያልሆነ ህዝብ ብዙ ነው። ጓዶች እውቀት ማለት እኛ የሰማነው እና የምናውቀው ብቻ አይደለም። እንዲያውም እኛ የማናውቀው ብዙ ነገር እንዳለ ማወቅ የእውቀት ጅማሮ ነው። ብዙ ሰዎች ዛሬ ላይ ስለ ዓለም፤ ስለ አገር፤ ስለ መንግስት፤ ስለ ኃይማኖት፤ ስለ ሌላውም እነሱ ጋር ያለው እውቀት የመጨረሻው እውቀት እንደሆነ በማመን በእርግጠኝነት ይናገራሉ። ይህ ስህተት ነው። እውቀት ተለዋዋጭ ነው። ነባራዊው ሁኔታም ተለዋዋጭ ነው። ሲስተምም መመሪያም ህግም ተለዋዋጭ ነው። ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ማወቅ እና መዘጋጀት እንጂ እኔ የማውቀው ብቻ ነው የመጨረሻው እውቀት ከዚያ ወዲህ አዲስ እውቀት አልመጣም ብሎ መታገል ስህተት ነው።

ሲጠቃለል፤ በመንግስት ተቋማት የምትሰሩ ሰዎች እባካችሁ ስንፍናችሁን በመመሪያ፤ በደንብ፤ በህግ፤ በሲስተም አንሸፍነው። ይልቁንም ወቅታዊውን መረጃ በትክክል ማወቃችንን እርግጠኛ እንሁን፤ ለማወቅም እንጣር። እንደ ህዝብ ደግሞ ለአዲስ እውቀት በራችንን እንክፈት፤ ያላወቅነው ነገር ሊኖር እንደሚችል በጥቂቱም ቢሆን እንጠርጥር።

ቸር እንሰንብት!

# ተስፋን የሰነቁ የሠላም ፍሬዎች...

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

አገራችን ኢትዮጵያ በእርቅ በተፈጠረ ሰላም ውስጥ ናት። የሁለት ዓመት የጦርነት ሰንኮፏን ጥላ በተስፋና በኃይል ብቅ እያለች ነው። የያዛትን የመገፋፋት መንፈስ አባርራ፣ የሸፈናትን የጥላቻ ደመና ጥሳ በልጆቿ የተስፋ ምስራቅ ላይ እያቀላላች ነው። ትንሽ ሰላም አንፈልግም። ላመል ሰላም አይበቃንም። የምንፈልገው ሰላም አስተማማኝና ዘላቂ..ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚተማመኑበትን ሰላም ነው።

ይሄ ሠላም ዋስትና እንዲያገኝ መንግስት ብቻ አይደለም፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ብቻ አይደሉም፣ እኔና የተወሰኑ ሰዎች ብቻ አይደለንም ሁላችንም ኃላፊነት አለብን። የጀመርነው ሰላም ሩቅ እንዲሄድ፣ አጽናፍ እንዲደርስ እኛ ወንድማማቾች ነን፤ ጥልና መገፋፋት አይበጀንም እንበል። የጀመርነው ሰላም እድገትና ብልጽግና፣ አንድነትና ከፍታ እንዲያመጣልን ጥላቻን በፍቅር እንግደለው። በልባችን ምስራቅ ላይ ያቅላላው የተስፋ ጭላንጭል በደመና እንዳይያዝ፣ በጉም እንዳይሸፈን ኃላፊነታችንን እንወጣ።

ብዙ ሰላም እንሻለን። ጥላቻን የሚገድል፣ መለያየትን የሚኮንን እልፍ ሰላም እንሻለን። አንድነትን የሚያመጣ ኢትዮጵያዊነትን የሚመልስ ብዙ ሰላም ግድ ይለናል። አዲሷ ኢትዮጵያ በትንሽ ሰላም የምትገነባ አይደለችም። ብዙ የፖለቲካ ነውር፣ ብዙ የፖለቲከኛ እድፍ ያቆሸሻት ናት። ብዙ ጥላቻ፣ ብዙ የትርክት ታሪኮች ያዛነፏት ናት። ብዙ እኔነት፣ ብዙ ራስወዳድነት ያጣመማት ናት። ብዙ ጦርነት፣ ብዙ ማንአለብኝነት ያጠየማት ናት። ይቺ አገር በትንሽ ሰላም አትቆነጅም።

ይቺ አገር በላመል ተስፋ፣ በቁራጭ እውነት አትነጻም። አስተማማኝ ሰላም ነው የሚያበጃት። አስተማማኝ ፍቅር ነው የሚበጀን። እንዴትም ሆነን አገራችን ዳግመኛ ወደጦርነት የማትገባበትን መላ መፍጠር አለብን፤ እንዴትም ብለን ማህበረሰባችን በፖለቲከኞቻችን ዕቃቃ ዳግመኛ እንዳይሰቃይ ማድረግ አለብን። እንዴትም ብለን መጪውን ትውልድ ከጥላቻና ከዘረኝነት መታደግ አለብን። እንዴትም ብለን በመነጋገርና በመግባባት የምታምረውን ኢትዮጵያ መፍጠር አለብን።

አገር እንደ ሠላም ውበት የላትም። ህዝብ እንደ ሠላም ደምግባት የለውም። ሠላም ያላቸው ነፍሶች ሁሉ ቆንጆዎች ናቸው። እናምር ዘንድ የክብር አክሊል የሆነውን ሰላም መቀዳጀት አለብን። የሠላም ስምምነቱ በሁለቱም ወገን ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎችን እያስተናገደ ነው። መንግስትም ሆነ ሕወሓት የገቡትን ቃል በመፈጸም ላይ ናቸው። ከሰሞኑ ተስፋችንን ከፍ ያደረገ ነገር በትግራይ ክልል ዋና ከተማ መቐለ እየተስተናገደ ይገኛል። የፌደራል መንግስት ልዑክ ቡድኑን ወደ መቀሌ ልኮ የሠላም ስምምነት ትግበራው ምን እንደሚመስል ክትትል አድርጎ ነበር።

በዚህ ሰቀን ሳናበቃ ወደ መቐለ የአየር በረራ ተጀመረ። ብዙ ሳቅ..ብዙ ደስታ ተስተናገደ። ከሰሞኑ የመቐለውን የአየር በረራ መጀመር አስመልክቶ የታየው የመንገደኞች ስሜት በማህበራዊ ሚዲያ ሲሰራጭ ነበር። ብዙ የትግራይ ተወላጆች ለሁለት ዓመት ከተለዩዋቸው ዘመድ ወዳጆቻቸው ጋር ሲገናኙ የነበረው የደስታ ስሜት እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አልነበረም። ናፍቆትና ደስታቸውን ከመተቃቀፍና ከመሳሳም ባለፈ በለቅሶ ሲገልጹ ነበር። ይሄን ነው የፈለግነው..ይሄ ነው የሚያስፈልገን።

የሰላም ፍሬዎች ሁልጊዜም ጣፋጮች ናቸው። በደስታና በእንባ የሚገለጡ ናቸው። ሰላም የገባበት ነገር ሁሉ ለሌላው ረፍት ነው። እነዛ ሳቆች.. እነዛ ፈገግታዎች ሰላም የወለዳቸው ናቸው። እነዛ እልልታዎች..እነዛ ፈንጠዝያዎች በእርቅ የተጸነሱ ናቸው። ለዓመታት በሰላም እጦት በጨፈገገ ፊት ላይ፣ በናፍቆትና በትዝታ በባባ ልብ ላይ ያን የሚያክል ጽኑ ሀሴት ማስተናገድ ከሠላም ውጪ ምንም እንዳናስብ የሚያደርግ ነው። ለሰላም መልፋት የቤት ስራችን ነው።

ሰላም እንዲህ ካሳቀን፣ መከራዎቻችን እንዲያስለቅሱን ለምን እድል እንሰጣቸዋለን? ልዩነት ሊኖረን ይችላል፣ እንደ ፖለቲከኛና እንደምናራምደው ርዕዮተ ዓለም ልዩነት ሊኖረን ይችላል፣ እኒህ ሁሉ ልዩነቶቻችን ግን ከአገርና ህዝብ የሚበልጡ አይደሉም። ፖለቲከኛ የሆነው፣ በሀሳብ ልዩነት የቆምነው ለህዝብ ስንል ከሆነ ለህዝብ ስንል ልንግባባና ልዩነቶቻችንን ማጥበብ ይኖርብናል። ለህዝብ ከሆነ የቆምነው፣ ለህዝብ ከሆነ የምንታገለው ስለህዝብ ስንል አንድ በሚያደርገን ነገር ላይ መግባባት ይኖርብናል። ለህዝብ ከሆነ የምንሟገተው፣ ለህዝብ ከሆነ የምንለፋው ለህዝብ ስንል መከራዎቻችንን በሰላም መቋጨት አለብን።

**የሰላም ፍሬዎች ሁልጊዜም ጣፋጮች ናቸው። በደስታና በእንባ የሚገለጡ ናቸው። ሰላም የገባበት ነገር ሁሉ ለሌላው ረፍት ነው። እነዛ ሳቆች.. እነዛ ፈገግታዎች ሰላም የወለዳቸው ናቸው**

በነገራችን ላይ ህዝብ ጦርነት አይፈልግም። የቱንም ያክል የሀሳብ ልዩነት በፖለቲከኞቻችን መሀከል ቢፈጠር ህዝብ ሰላምን እንጂ ጦርነትን አይፈልግም። እስካሁን ድረስ ያስተናገድናቸው ጦርነቶች በጥቂት ቡድኖች ፈቃድ እንጂ በብዙሀኑ ፍቃድ የሆነ አይደለም። ለህዝባችን ልንሰጠው የሚገባን ብቸኛው ነገር ሰላም ነው። እንደ ፖለቲከኛም ሆነ እንደ ማንኛውም ዜጋ ለአገራችን ልናውለው የሚገባ ተቀዳሚው ውለታ የሰላም ውለታ ነው። የሰላም ውለታ ደግሞ በእርቅና በይቅርታ፣ በውይይትና በወንድማማችነት የሚገለጽ ነው። የሰላም ውለታ አሁን አገራችን ላይ እየሆነ እንዳለው የሰላም አማራጮችን በማስፋትና በዛ እውነት ውስጥ በመመላለስ የሚገለጽ ነው።

አሁን ጊዜው በሰላም ሀሳብ ኢትዮጵያን የምንክስበት ነው። አሁን ጊዜው በእርቅና በይቅርታ ቆሜልሀለው የምንለውን ህዝብ የምናገለግልበት ነው። ህዝብ በፍቅር ካልሆነ በምንም አይገለገልም። ከፍቅር ውጪ ልናገለግለው ብንሞክር እንኳን ጥሩ ነገር አንሰጠውም። አገር በሰላም ካልሆነ በምንም አትገለገልም። ከሰላም ውጪ በሆነ መንገድ ልናገለግላት ብንሞክር አንጠቅማትም።

አገራችንንም ሆነ ህዝባችንን በሰላም ሀሳብ የምናገለግልበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን። ይሄን ጊዜ ለሰላም ካልሆነ ለሌላ ለምንም ልንጠቀመው አይገባም። ይሄን ጊዜ ለአንድነትና ለወንድማማችነት ካልሆነ ለሌላ ለምንም ልንጠቀመው አይገባም። ይሄን ጊዜ በሰላም እጦት የባከኑብንን በረከቶቻችንን ለመመለስ ካልሆነ ለሌላ ለምንም ልንጠቀመው አይገባም።

በሠላም ቤት እንስራ። እንደ አገር..እንደ ዜጋ ለሁለት ዓመታት ሁሉንም ዓይነት መከራ ስናስተናግድ ነበር። ትንሽ ዞር ማለት አቅቶን..ትንሽ ማሰብ ተስኖን በማይመጥነንና በማይገባን ስፍራ ላይ ነበርን። አሁን እንደ አገር አሸንፈናል። አንድነታችን እንደሚበልጥ ተረድተን፣ ፍቅር እንደሚሻለን ተምረን መደናቅንው እውነት ተመልሰናል። አትችሉም ላሉን፣ ከጦርነት ውጪ እውቀት የላቸውም ለሚሉን፣ እንድንባላና እየተገዳደልን እንድንኖር ከኋላ ሆነው በለው ለሚሉን ጠላቶቻችን ችግርን በመነጋገር ፈትቶ አብሮ መኖር እንደሚቻል አሳይተናል። አሁን ጊዜው በፍቅር ወደፊት የምንራመድበት ነው። በጋራ የፈጠርናቸውን ችግሮቻችንን በጋራ መፍትሄ እየሰጠን የጋራ አገር የምንሰራበት ነው።

መንግስት ለሰላም ያለውን ጽኑ ፍላጎት በተለያየ ጊዜ አሳይቶናል። ለሰላም የተዘረጋ እጁ መቼም እንደማይታጠፍ ከቃል ባለፈ በተግባር አስተውለናል። በገባው ቃል መሰረት ሁሉም በመፈጸም ላይ ነው። እያየነው ያለው ነገር እጅግ ተስፋ ሰጪ ነው። በሰላም ስምምነቱ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሁሉም ነገር ጊዜውን ጠብቆ ሰላም ፈጣሪ በሆነ መንገድ እንደሚቀጥል እናምናለን። ከሁለቱም ወገን ማለትም ከሕወሓትም ከፌደራል መንግስትም የሰላም ስምምነቱ የሚፈልገው ነገር ሁሉ በመፈጸም የጓጓንለትን ሰላም የምናጣጥምበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ሠላም ይርባል..እሾህን በእሾህ እንዲሉ የሰላም ርሀብ በራሱ በሰላም ካልሆነ በምንም አይፈወስም። እንደ እኛ በሰላም ርሀብ የተንሳቆለና የከሳ የለም። ስለሰላም ለማውራትም ሆነ ለመጻፍ ከእኛ የተሻለ የሚያውቅ አለ ብዬ አላስብም። ሰላም በደንብ የገባን በደንብ ስለተሰቃየንበት ነው። በደንብ የተረዳነው በደንብ ስለተራብነው ነው። ጎምርቶና ፍሬ አፍርቶ ወደ መሬትም ወርዶ የርሀባችንን ያክል፣ የጉስቁልናችንን ያክል እስከንዋሃደው ድረስ ለሰላም ማንኛውንም መስዋዕት መክፈል ይጠበቅብናል።

ተስፋን የሰነቁ የሰላም ፍሬዎች ያስፈልጉናል። ህመሞቻችን በነሱ ነው የሚድኑት። ቁስሎቻችን በነሱ ነው የሚሽሩት። በሰላም አማራጮች ለቁስሎቻችን መድሀኒት እንጂ ጥዝጣዜ መሆን የለብንም። እስከዛሬ በሚያስፈልገን ልክ ለሰላም ለፍተን አናውቅም። እርግጥ ስለሰላም አውርተንና ለፍልፈን እናውቅ ይሆናል ሰላም ለማምጣት ግን ብዙ ርቀት ተጉዘን አናውቅም።

አብዛኞቻችን ከተግባር ይልቅ ለወሬ ቅርብ የሆነ ማንነት ነው ያለን። እስከዛሬም ሰላማችንን የሰወርነው ከቃል ያለፈ የትግበራ አቋም ስለሌለን ነው። ሰው አዋቂና አስተዋይ ከሆነ ስለሰላም ማውራት ብቻ ሳይሆን ስለሚመጣበት መንገድም ማሰብ አለበት። የአሁኑ የሰላም ተስፋችን ከወሬ ባለፈ የወሰድነው የተግባር ውጤታችን ነው። ከዚህ በኋላም ለሚኖሩብን አገራዊና ግለሰባዊ ችግሮች ከወሬ ባለፈ ለተግባር የሚሆን ቁመና ያስፈልገናል።

ለህመሞቻችን መድሃኒት ከመፈለግ ይልቅ ህመሞቻችንን እሽሩሩ ማለት የሚቀለን ነን። ብዙ ግዜ መፍትሄ ላይ ከማተኮር ይልቅ ችግሮቻችን ላይ ማተኮር የሚቀናን ነን። ሰላምን አምጦ መውለድ ያቃተንም ለዚህ ነው፤ አሁን የተወለደው ሰላም በብዙ ምጥ ነውና እንደ ዓይናችን ብሌን ልንጠብቀው ይገባል። በጋራ ኃላፊነት፣ በጋራ ተቆርቋሪነት ትንሽዋ ሰላም ከፍ ማድረግ ከእኛ ይጠበቃል።

ሠላም ቡቃያ ነው.. አድጎና መንድጎ ዋርካ እስኪሆን ድረስ ክትትል ይፈልጋል። ሠላም ችግኝ ነው..አድጎና መንድጎ ስር እስኪሰድ ድረስ እንክብካቤ ያሻዋል። በዚም ሆነ በዛ የተጀመረው ተስፋ ሰጪ ሰላም አብቦና እሸት አሽቶ መከራዎቻችንን እስኪያስረሳን ድረስ ተስፋ ማድረጋችን ይቀጥላል። በኢትዮጵያ ምድር እንዲሆን የምንፈልገው እድገትና ብልጽግና፣ ለውጥና ስኬት ሰላምን ተደግፎ የሚሆን ነውና ስለ ሰላም ዝም አንልም።

ተስፋን የሰነቁ የሰላም ፍሬዎች..የአገር ሰብል፣ የህዝብ አዝመራዎች ናቸው። በእኛው ተተክለው በእኛው የሚጸድቁ። የሠላም ፍሬዎቻችን እንዳይጠወልጉ ውሀ ማጠጣት፣ ማዕድን ማስታቀፍ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ተስፋ ካለመኖር ወደመኖር የምንሸጋገርበት ድልድይ ነው። ማንም ሰው በዚህ ድልድይ ላይ ሳይራመድ ወደ ዛሬና ወደ ነገ መሄድ አይችልም። ማንም ሰው በዚህ ድልድይ ላይ ሳያልፍ መኖር አይችልም።

የተስፋ አብራክ ሰላም ነው። ተስፋ በሰላም ውስጥ ተረግዞ ሲወለድ ነው መኖር የሚጣፍጠው። ተስፋ በእርቅና በፍቅር ሲጸና ነው ህይወት የሚያጓጓው። አሁናዊው የአገራችን ገጽታ ከዚህ እውነት ጋር ልክክ ያለ ነው። አገራችን ለሁለት ዓመታት ሠላምና ፍቅር፣ አንድነትና ተስፋ ርቋት ነበር። አሁን ያጣነውን ሠላም አግኝተነዋል።

ከጦርነት ይልቅ ሠላምን፣ ከመገፋፋት ይልቅ መነጋገርን አስቀድመን ወደቀደመ ክብራችን እንመለስ። አሁንም ገና ነን፤ ስለሰላም ብዙ ይቀረናል። እየታየ ያለው የሰላም ጭላንጭል ዋርካ ሆኖ ጥላ እስኪያጠላልን ድረስ ለሠላም መድከማችን ይቀጥላል። የሆነ ቀን ላይ ፍቅር ባልነካው ልብ ተቀያይመን ነበር። የሆነ ቀን ላይ በወንድማማቾች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ተስፋችንን፣ ዕምነታችንን፣ ሠላማችንን አጥተን ነበር። አሁን ወደዛ ወዳጣነውና ስንፈልገው ወደነበረው መንፈስ ተመልሰናል።

ጥልን ገሎ በፍቅር መተቃቀፍ እንዴት ደስ ይላል? ቂምን ረስቶ በሠላም መጨባበጥ እንዴት ያረካል? አገሬ የሚያስፈልጋት ይሄ ነው። አሁን ጊዜው ሞትን የምንገልበት ጊዜ ነው። አሁን ጊዜው ጥላቻን አርቀን የምንጥልበት ሰሞን ነው። ሞት ይሞታል.. የሞት ሞቱ ሠላም ነው። ሞትን እንግደለው..ጥላቻን እናሳፍረው።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## የአርሶ አደሩን ተሳትፎ የሚጠይቀው የዘርያ ማሻሻል ስራ

**ስምስም መንግሥቱ**

ግብርናው አሁንም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ሰፊ ድርሻ ይዞ ይገኛል። መንግስትም ለእዚህ ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። የምግብ ዋስትናን እንዲሁም የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ ከግብርናው ዘርፍ የወጪ ንግድ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው ቀጥለዋል። የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በመንግስት፣ በግብርናው ዘርፍ አካላት፣ በአርሶ አደሩና በሌሎች የዘርፉ አካላት እየተደረገ ባለው ርብርብ ከዘርፉ የሚገኘውን ምርት ማሳደግ ተችሏል። ግብርናው በአጠቃላይ የአገር ውስጥ ገቢ ያለው ድርሻም አሁንም ከፍተኛ መሆኑን ቀጥሏል።

እንዲያም ሆኖ ግን የግብርና ምርቶች የአቅርቦትና ፍላጎት ክፍተት ይስተዋላል፤ ይህን ክፍተት ለመሙላት አሁንም ርብርብ እየተካሄደ ይገኛል። በአገሪቱ በመኸርና በበጋ መስኖ እየተካሄደ ያለው የስንዴ ልማትም ከዚሁ አኳያ የሚታይ ነው። ግብርናውን ለማዘመን፣ የተሻሻለ ዘርያ እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች መጠቀም ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራም ነው።

በተለይ የተሻሻለ ዘርያ ከመጠቀም አኳያ ብዙ ርቀቶች ተሄደዋል። ቴክኖሎጂው በሄክታር የሚገኘውን ምርት በወሳኝ መልኩ መጨመር አስችሏል። አርሶ አደሩም የቴክኖሎጂዎቹን ፋይዳ እየተገነዘበ መምጣቱን ተከትሎ ምርትና ምርታማነቱ የዚያኑ ያህል እያደገ ነው። ይህንንም የዘርፉ ባለሙያዎች እያረጋገጡ ናቸው።

የዘርፉ ባለሙያዎች የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በማምጣት የተሻሻለ ምርጥ ዘር መጠቀምን ማበረታታቸውን ቀጥለዋል። የባለሙያዎችን ምክረ ሀሳብ ተቀብለው፣ በመንግሥት ድጋፍና ክትትል የምርትና ምርታማት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂ የተጠቀሙ አርሶ አደሮች ውጤታማ ስለመሆናቸው የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። የመስክ ጉብኝቶችና የተሞክሮ ልውውጦችም ይህንኑ እያረጋገጡ ናቸው። በዚህም አንዱ አርሶ አደር ከሌላው እንዲማር እየተደረገ ነው።

የተሻሻለ ዘርያ መጠቀም ባህል እያደገ የመጣው ብዙ ፈተናዎች ታልፈው ነው። በቴክኖሎጂው አጠቃቀም ላይ የአመለካከት ልዩነት ሲስተዋል ቆይተዋል። ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አለመፍጠን ይስተዋላል። የተሻሻለ ዘርያ ከነባሩ ዘርያ ይልቅ ለበሽታ ይጋለጣል የሚል ስጋት ያላቸው አርሶ አደሮች ነበሩ፤ አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎችም ከጥቅሙ ይልቅ ክፍተቱን ይዘው የሚሰጡት መረጃ በአርሶ አደሩ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳርፏል። በጣእም እና በንጥረ ነገር/ኦርጋኒክ መሆን አለመሆን/ላይ ልዩነት ስለመኖሩ ሊናገሩ የሚችሉት አርሶ አደሮች ሳይሆኑ እነዚህ የዘርፉ ባለሙያዎች ናቸውና።

የኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ጉምቢቹ ወረዳ ነዋሪውና በግብርና ሥራ የሚተዳደሩት አቶ ከበደ ሸዬ፤ የተሻሻለ ዘርያ ለምርታማነት የሚመረጥ እንደሆነ ያምናሉ፤ አጠቃቀሙ ግን ነባር ዘርያን በተሻሻለ ዘርያ በመተካት ወይንም ነባር ዘርያው እንዲጠፋ በማድረግ መሆን የለበትም የሚል አቋም አላቸው።

ስጋቱም አስፈላጊነቱም ተገቢ ነው የሚሉት የግብርናው ዘርፍ ተመራማሪና አማካሪ ዶክተር አምሳሉ አያና አሁን ላይ እየጨመረ የመጣውን የህዝብ ብዛትና ፍላጎት ለማሟላት ምርታማነትን መጨመር የግድ እንደሆነ ነው የገለጹት። የተሻሻለ ዘርያ የተሻለ ምርት እንደሚሰጥም በመግለጽ፤ ነባር ዘርያንም የመጠበቁ ተግባር እየተሰራበት መሆኑን ይናገራሉ።

የነባር ዘርያን አስፈላጊነት አበክረው የተናገሩት አቶ ከበደ በተለይ በአካባቢያቸው እጅግ ተፈላጊ የሆነ ለፓስታ ግብአት የሚሆን ነባር ዘርያ ጥቁር ስንዴ መኖሩን በማስታወስ፣ስንዴው በአንድ በጎፈቃደኛ ግለሰብ አማካኝነት ናሙናው ጣሊያን አገር ተልኮ ለፓስታ አስፈላጊ መሆኑ መረጋገጡን ያስረዳሉ።

አቶ ከበደ መንግሥት ትኩረት እየሰጠ ያለው ለተሻሻለ ዘርያ እንደሆነ በመጥቀስ፣ ይህ ስንዴ በአሁኑ ጊዜ ዘርያው እየቀነሰ እንደመጣና ጥበቃ ተደርጎለት ዘሩ እንዲስፋፋ ካልተደረገ ጭርሱኑ ሊጠፋ ይችላል የሚል ስጋት እንዳደረባቸው ይናገራሉ።

የተሻሻለ ዘርያ ያላቸው ሰብሎችን ለተከታታይ ዓመታት ለማምረት አስቸጋሪ እንደሆነም በመጥቀስ፣ በበሽታ የመጠቃት እድሉ ሰፊ እንደሆነ ነው ያስረዱት። ነባር ዘርያዎች ግን ዘመናትን የመሻገር አቅም እንዳላቸው ተናግረው፣ እርሳቸውም በሶስት የመንግሥት ስርአት ውስጥ ሲያሳልፉ ነባር ዘርያዎች እንዳልጠፉና ዛሬም ድረስ መኖራቸውን ነው የገለጹት። ዘርያዎቹ ገበያ ላይም ተፈላጊ እንደሆኑ ተሞክሮአቸውን አካፍለውናል።

ነባር ዘርያ ለምርትና ምርታማነት እድገት አስተዋጽኦ አያደርግም የሚለውን ሀሳብ አቶ ከበደ አይቀበሉም። ጉድለቱ ከአርሶ አደሩ አጠቃቀም ላይ መሆኑን በመግለፅም ዘርያውን ማከም ከተቻለም ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል ይላሉ። ኋላቀር ነው እየተባለ ነባር ሀብት በምርጥ ዘር ወይንም በተሻሻለ ዘርያ እየተተካ ነው። የሚያዋጣው ነባሩንም የተሻሻለ ዘርያንም ጎን ለጎን ማስኬድ ወይንም መጠቀም ነው ሲሉ ያመለክታሉ።

አቶ ከበደ እርሳቸውን ጨምሮ ለነባር ዘርያ ተቆርቋሪ የሆኑ የአካባቢያቸው ነዋሪዎች ተነሳሽነት ወስደው ለነባር ዘርያዎች ጥበቃ ለማድረግ መንቀሳቀሳቸውንም ገልጸውልናል። አቶ ከበደ እንደነገሩን ጥቂት አርሶ አደሮች ሆነው በአካባቢያቸው ‹‹ጨፌዶንሳና አካባቢው የነባር ዘር ተንከባካቢ ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር›› የሚል ስያሜ ያለው ህጋዊ ማህበር መስርተዋል። የማከማቻ መጋዘን ገንብተው የተለያዩ የሰብል ዘርያዎች በመሰብሰብ ለዘርያዎቹ ጥበቃ ማድረጋቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ይህ ስራቸው በአንዳንዶች ትችት ገጥሞት እንደነበር አርሶ አደሩ ይናገራሉ። ውጤቱን ተመልክተው አስፈላጊነቱን እየተገነዘቡ የማህበሩ አባል ለመሆን ፍላጎት የሚያሳዩ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። በ72 አርሶ አደሮች የተጀመረው እንቅስቃሴ ከአንድ ሺ በላይ አባላትን በማፍራት ይበልጥ ተጠናክሯል። በአሁኑ ጊዜ አባላትን በማፍራት ችግር የለበትም። ችግሩ ከአባላት የሚሰበሰብ ነባር ዘርያ ማስቀመጫ የሚውል መጋዘን ጥበት ሆኗል።

እነ አቶ ከበደ ዘርያዎችን ጠብቆ ለማቆየት የሚያስፈልጉ አስፈላጊ ነገሮችን ከኢትዮጵያ ብዝሓ ሕይወት ኢንስቲትዩት ግንዛቤ አግኝተው ነው ወደ እንቅስቃሴ የገቡት። ከኢንስቲትዩቱ ጂን ባንክ የተወሰኑ የዘርያ ናሙናዎችንም አግኝተዋል።

ነባር ዘርያዎችን ተደራጅተው ለማባዛት ፍላጎት ያሳዩ በጉምቢቹ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ 12 ቀበሌ ገበሬ ማህበራት ውስጥ የሚገኙ አርሶ አደሮች የማህበሩ አባል ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆኑ፣ በአሁኑ ጊዜም ሴት አርሶ አደሮችን ጨምሮ ከአንድ ሺ500 በላይ አርሶ አደሮች የማህበሩ አባል ሆነዋል።

ማህበሩ ከ20 ሚሊየን በላይ ካፒታል አፍርቷል። ማህበሩ ካፒታሉን ለማሳደግ ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ፤ አንድ ኩንታል ስንዴ በብድር ሲሰጥ፤ 20 ኪሎ ግራም ወለድ በመሰብሰብ ነው። አዲስ አባል አርሶ አደሮችን በማፍራትና ለአባላቱ ዘርያ በመስጠት እንዲስፋፋ ማድረግ ሌላው የሚጠቀምበት ዘዴ ነው።

አሁን ላይ በአካባቢያቸው ‹‹ማንጉዶ›› የተባለ የተሻሻለ ዘርያ ያለው ለፓስታና ማካሮኒ የሚውል ስንዴ ከነባር ዘርያ የተገኘ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ከበደ፣ በኦሮምኛ ስያሜ የተሰጠው የስንዴ ዘር አንጋፋ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑንም አስረድተዋል። አቶ ከበደ መንግሥት ሊያግዛቸው እንደሚገባም ነው መልእክት ያስተላለፉት።

ነባር ዘርያ ላይም ሆነ የተሻሻለ ዘርያ ላይ በአቶ ከበደ የተነሳው ሀሳብ ተገቢነት እንዳለው የገለጹት የዘርፉ ተመራማሪና አማካሪ ዶክተር አምሳሉ አያና፤ በዚህ ወቅት ዓለምም እየተጠቀመበት ያለው በተሻሻለ ዘርያ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ነው ይላሉ። ኢትዮጵያ ውስጥም የህዝብ ብዛት እየጨመረ፣ የምርት ፍላጎትም እያደገ በመሆኑ ይህን ለማጣጣም ምርታማ መሆን ይጠበቃል ሲሉ ይገልጻሉ።

ዶክተር አምሳሉ እንደሚሉት፤ ምርታማ ለመሆን ደግሞ በዘርያ ማሻሻያ ዘዴ ወይንም ሳይንስ በመጠቀም በስፋት ጥቅም ላይ ማዋል ይጠበቃል። የተሻሻለ ዘርያ በአንድ ሄክታር የተሻለ ምርት ስለሚሰጥ ተገቢ ሚና

> **አርሶ አደሩ ዘንድ ያለውም እውቀት መጠበቅ አለበት የሚለው አስተሳሰብ ተገቢነት አለው። በግብርናው ሥራ መሆን ያለበት ይህን ምረጡ፤ ያንን ተው ማለት ሳይሆን፣ ሁለቱን አጣጥሞ መተግበር የሚቻልበትን መንገድ መከተል እንዲሁም የትኛውን ዘርያ በየትኛው ቦታ መጠቀም የሚለውን መለየት ነው**

ይጫወታል። በመሆኑም የተሻሻለ ዘርያ መኖሩ የግድ ነው።

አርሶ አደሩ ዘንድ ያለው እውቀትም መጠበቅ አለበት የሚለው አስተሳሰብም ተገቢነት አለው ይላሉ፤ ዶክተር አምሳሉ። በግብርናው ሥራ መሆን ያለበት ይህን ምረጡ፣ ያንን ተው ማለት ሳይሆን፣ ሁለቱን አጣጥሞ መተግበር የሚቻልበትን መንገድ መከተል፤ እንዲሁም የትኛውን ዘርያ በየትኛው ቦታ መጠቀም የሚለውን መለየት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

ዶክተር አምሳሉ እንዳሉት፤ በዘርያ ማሻሻያ ወቅት ችግሮች የሚያጋጥሙት አርሶ አደሩን ሳያሳትፉ በማበልጸግ ጥቅም ላይ እንዲውል ሲደረግ ነው። በምርምር ሥራ ወቅት አርሶ አደሩን ማሳተፍ ያስፈልጋል።

በእርሳቸው ተሞክሮ የማሽላ ምርታማነትን ለመጨመር የዘርያ ማሻሻያ ለማድረግ በወሎ እና ሐረርጌ የዘርያ ማሻሻያ ምርምር ባካሄዱበት ወቅት የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ነበር ምርምር ያካሄዱት። በአርሶ አደሩ አሰራር ላይ የተወሰነ ሳይንስ በመጨመር እንጂ ሙሉ ለሙሉ የመቀየር ምርምር አልነበረም የተደረገው።

በዚህም በሁለቱ አካባቢዎች ጥሩ ዘርያ ያለው ምርት የሚሰጥ ማሽላ ማስገኘት ተችሏል። የአካባቢው አርሶ አደር የሚያመርተውን ማሽላ ስንዴ ለምኔ፣ ወተት በጉንጬ የሚል ስያሜ እንዳወጣለትም ገልጸዋል። በትግራይ አካባቢም በአካባቢው ደቆቆ ተብሎ ከሚጠራው ሰብል የሚዘጋጀው ለሽሮ ወጥ የሚውለው ዘርያም እንዲሁ በገበያ ላይ ተመራጭ ሆኗል። ዋጋው ከሌላው የሚጨምር በመሆኑ አርሶ አደሩን በገቢ ተጠቃሚ አድርጎታል። አርሶ አደሩን ያሳተፈ የምርምር ሥራ ውጤታማነቱ የጎላ እንደሆነ እነዚህ ተሞክሮዎች ማሳያዎች ናቸው።

በጤና ላይ ሊከሰት የሚችልን ስጋት ለመከላከልም ኦርጋኒክ የሆኑ ምርቶች እንዲመረቱ በምርምር ሥራው ማድረግ የሚቻልበት እድል መኖሩን የጠቆሙት ዶክተር አምሳሉ፤ የአፈር ለምነትን የሚያሻሽልና ማሳን የሚያዳብር ኮምፖስት በመጠቀምና ሰብልን አፈራርቆ በመዝራት ዘዴ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል። ዶክተር አምሳሉ ላቲን አሜሪካ ያለውን ተሞክሮ አስመልክተው እንደገለጹትም፤ በቆሎ ይዘራል፤ ከበቆሎው አጠገብም በቆሎው ላይ ሊጠመጠም የሚችል የቦለቄ አይነት ዘርያ ያለው አብሮ ይዘራል፤ ዱባ ይተከላል። የዱባው ተክል መሬቱን ይሸፍናል። ጥራጥሬዎች ናይትሮጂን የተባለውን ንጥረ ነገር አፈር ውስጥ የመጨመር ፀባይ ያላቸው በመሆኑ ሶስቱ ሰብሎች የመሬቱን ለምነት ለመጠበቅ ያግዛሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ በአጠቃላይ ከተሻሻለ ዘርያ አቅርቦት ጋር ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ዶክተር አምሳሉ ላቀረብንላቸው ጥይቄ በሰጡት ምላሽ፤ የምርምር ሥራው ነባሩን ዘርያ ያገለለ አይደለም። በመንግሥት በተቋቋመ ተቋም ውስጥ ከመላ አገሪቱ የተሰበሰቡ ዘርያዎች እንዲጠበቁ እየተደረገ ነው። ተመራማሪዎችም ከዚህ ተቋም ዘርያዎችን በመውሰድ ማሻሻያ በማድረግ እንዲለቀቁ ይደረጋሉ። የተወሰኑ ዘርያዎች ከውጭ ሊቀርቡ ይችላሉ። ነገር ግን የጤፍና ቡና ዘርያዎች የኢትዮጵያ ብቻ ናቸው። የተሻሻሉ ዘርያዎች የሚወጡ እንኳን ቢሆን መነሻው ነባር ዘርያ ነው። በአርሶ አደሩ እጅ የሚገኝ ዘርያን ማሻሻል የግድ ነው።

የተሻሻለ ዘርያ ያላቸው በቀላሉ ለበሽታ ተጋላጭ እንደሆኑ ስለሚነሳው ሀሳብም ዶክተር አምሳሉ ሲያብራሩ ‹‹እንዲህ ያለው ችግር የሚፈጠረው እያሻሻልን በሄድን ቁጥር በዘረመል የመቀራረብ ባህሪያቸው ከፍተኛ እየሆነ ይሄዳል›› ይላሉ። ይህንንም በምሳሌ ሲያብራሩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የስንዴ ዘርያዎች በጣም የተሻሻሉ በመሆናቸው በዘረመል የመመሳሰል ነገር ተፈጥሯል ሲሉ ይገልጻሉ። በዚህም በበሽታ የመጠቃታቸው ሁኔታ እየጨመረ ነው፤ ስለዚህ በሌላ ዘርያ ይተኩ የሚል ሀሳብ እየቀረበ ነው፤ ይህም የማይቀር ነው ይላሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ አንዱ በበሽታ ሲጠቃ በሌላ ለመተካት ከበፊተኛው የተሻለና በሽታን መቋቋም የሚችል መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ ግብአት ያስፈልጋል። ሌላ ዘረመል የሚገባ በመሆኑ ግብአት ያስፈልጋል። በመስክና በላቦራቶሪ ውስጥ የተጠበቀ ዘርያን በማዳቀል ዘዴ ነው የሚከናወነው። በማዳቀል ዘዴ ድርቅ መቋቋም መቻሉና ጥሩ የምግብ ጣዕም ያለው መሆኑ ይፈተሻል። የእጽዋት ማበልጸጊያ ቦታ በማስፋፋት ጭምር ነው ምርምሩ እንደሚከናወን አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር አምሳሉ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ታዳጊ ተብለው ከሚጠሩ አገሮች መካከል በግብርና ምርምር ጥሩ ፕሮግራም ካላቸው ውስጥ አንዷ ሆና ትጠቀሳለች። በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ የምርምር ተቋማት ተቋቁመው እየሰሩ ናቸው፤ ዩኒቨርሲቲዎችም በምርምር ያግዛሉ። ይህ አስፈላጊና መልካም ተሞክሮ ነው።

የኢትዮጵያ የብዝሃ ሀብት ኢንስቲትዩት፣ የፌዴራልና የክልል የምርምር ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ተጣምረው በመናበብ የበለጠ ውጤታማ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ያስገነዝባሉ። ይህም አርሶ አደሩን ያሳተፈ የዘርያ ማሻሻል ስራ ለመሥራት ይረዳል። ከአርሶ አደሩ ጋር የተሰራው የዘርያ ማሻሻያም ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበታል። በዚህ መልኩ ተመርቶና ገበያ ላይ ውሎ ተመጋቢው ዘንድ እስኪደርስ ያለው ሂደት መቀጠል ይኖርበታል። የእሴት ሰንሰለቱ ተጠናክሮ ከቀጠለ ምርት ተቀብሎ የተለያየ እሴት በመጨመር ለተጠቃሚው ለሚያቀርበው የሥራ እድል ይፈጥራል። በግብርናው ዘርፍ አገራዊ ኢኮኖሚን ማሳደግ የሚቻለው በዚህ መንገድ መንቀሳቀስ ሲቻል ነው። በአጠቃላይ ከዘርያ ጋር በተያያዘ የተጠናከረ ሥራ ይጠበቃል ሲሉ ዶክተር አምሳሉ ሀሳብ ሰጥተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ‹‹ችግር ብቻ ማየት ከስህተት አይመልስም››

**- አቶ ዳዊት አዘነ**
**የትምህርት መሰረተ ልማትና አገልግሎቶች ዴስክ ኃላፊ**



**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ጦርነት ለማንም የሚበጅ አይደለም። መጀመሪያ ራስን ከዚያም ቤተሰብን በመቀጠል ደግሞ አገርን ይጎዳል። ለዚህም ማሳያ የምትሆን ሶርያ ናት። ብዙዎች ሳይወጡ በዚያው ቀርተዋል። የቻሉ ደግሞ የሚሸሹበትን ፈልገው እኛ ድረስ ዘልቀዋል። አገር የሌለው ሰው ደግሞ ምን እንደሚደርስበት እነርሱ አይተን መናገር እንችላለን። ‹‹ብልጥ ሰው ከሌላ ይማራል›› እንዲል ብሂሉ ከሌላ መማሩ ይሻላል። በየጊዜው የምንጋጭበትን ነገር ማቆምን አሁን መጀመር አለብን። ምክንያቱም በዚህ ግጭት ሳቢያ ብዙዎች ሕይወታቸው ጭምር አጥተዋል፤ ተፈትነዋል፤ ለመኖርም እያቃታቸው ነው።

አገርም እንደ አገርም ቢሆን ከባድ ችግር ውስጥ ገብታለች። ስለሆነም ለምንኖርባት፣ ለምንመካባት አገራችን ሲባል አትርፈን ለመስራት እንጂ ለመጨቃጨቅ ጊዜ አንስጠው። ወደፊት ለመራመድ የፈረሰውን ማነጽ ያስፈልጋልና ግዴታችን እንደሆነ አምነን ይህንን እናድርግ።

ለዛሬው የአስኳላ አምዳችን በትምህርቱ ዘርፍ ላይ ያለውን ፈተናና የመልሶ ግንባታ ጉዳይ ልናነሳ ወደናል። ይህንን የሚያብራሩልንና ስለ ጉዳዩ የሚነግሩን ደግሞ በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት መሰረተ ልማትና አገልግሎቶች ዴስክ ኃላፊ አቶ ዳዊት አዘነ ናቸው። አቶ ዳዊት ያካፈሉንን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡-

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የነበረው ግጭት ዘርፉን በብዙ መልኩ ጎድቶት ቆይቷል። ቢሆንም ግን ዝም አልተባለምና ወደሥራ ተገብቷል። ሰላሙን ተከትሎ ምን አይነት ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው፤ በምንስ ያህል ፍጥነት እየተጓዘ ነው?**

**አቶ ዳዊት፡-** እንደተባለው በግጭቱ ምክንያት የመጡ ችግሮች ዘርፈ ብዙ ናቸው። በዚህም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተለይም በአማራና አፋር ክልል የወደሙትን ከ1ሺ300 በላይ ትምህርት ቤቶች መልሶ ለመገንባት በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ነን። በኦሮሚያና በቤኒሻንጉልም እንዲሁ እንደ ሁለቱ ክልሎች ባይሆንም ትምህርት ቤቶች በመውደማቸው ያንንም መልሶ ለመገንባት እየተሰራ ይገኛል። በተጨማሪ በእነዚህ ክልሎች በከፊል የወደሙ ከአራት ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። በዚህ ምክንያት ደግሞ ከሦስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጪ ሆነው ቆይተዋል። እናም እነርሱን ወደ ትምህርት ገበታቸው ለመመለስ ከፍተኛ ወጪ ቢጠይቅም የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ናቸው።

መንግስት ተግባሩን ብቻውን ለመከወን ያዳግተዋል። ስለሆነም ሥራውን በጋራ ለማከናወን የልማት አጋር ድርጅቶችን የማሳተፍም ሥራ ተጀምሯል። በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የዚህ ሥራ አካል እንዲሆኑ እየተደረገም ነው። አሁን በዋናነት የሀብት ማሰባሰቡና የዲዛይን ሥራዎች በአብዛኛው እየተከናወነ ያለው በዚህ መልኩ ነው። መልሶ ግንባታው ሲታሰብ የወቅቱን የትምህርት ደረጃ የጠበቀ መሆን እንዳለበት ታምኖበታል። በዚህም ሙሉ የወደመውን ትምህርት ቤት በአንድ ጊዜ ለመስራት አይቻልም። ነገር ግን በዓመት በዓመት እየከፈሉ የተወሰነውን እየሰሩ የተሻለውን ማምጣት ላይ ለመድረስ ታስቧል፤ ይህ ደግሞ ጅማሮዎች እየታዩበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጅማሮው የደረሰውን አጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ችግሮች በምን ያህል እንደሚፈታው ያመላክታል?**

**አቶ ዳዊት፡-** ትምህርት ሚኒስቴር ግጭቱ የነበረባቸውን አካባቢዎች በሙሉ መሰረት በማድረግ በዘርፉ ላይ ያሉ ችግሮችን እልባት እንዲያገኙ ከማድረግ አኳያ አብይ ኮሚቴና ንዑስ ኮሚቴ አቋቁሞ እየተንቀሳቀሰ ነው። በተለይ በቅርቡ የተለቀቁትን የአማራና አፋር ክልሎች፣ ትግራይ ክልልን የሚመለከት በከፍተኛ አመራሩ የሚመራ አብይና ንዑስ ኮሚቴ እንዲሁም በባለሙያ የሚመራ የተለያዩ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል። ይህ ኮሚቴ ደግሞ በአገር ደረጃ የተቋቋመውም አባል ነውና ጅማሬው በጠንካራ መሰረት ላይ ያረፈ በመሆኑ ወደፊት የሚመጣውን መልካም ውጤት ያሳየናል። በሚወርደው አቅጣጫ መሰረት በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ እንዲቀጥሉም ያስችላልና ስኬታማ ያደርገናል። በተለይም ዕቅድ ተዘጋጅቶ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ መምጣቱ ጥሩ ነገር ለመምጣቱ ማሳያ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዕቅዱ ከመልሶ ግንባታው አንጻር ሲተነተን ምን ያህል ትምህርት ቤቶች በዓመት ውስጥ ይሰራሉ ተብሎ ታስቧል፤ በማንስ ይከናወናል?**

**አቶ ዳዊት፡-** ሙሉ ለሙሉ የወደሙትን እንዲገነባ የተወሰነው በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት ነው። በከፊል ውድመት የደረሰባቸውን ደግሞ ክልሉ በራሱ ጠግኖ ወደ ሥራ እንዲያስገባ የሚል ሀሳብ ነው ያለው። እንቅስቃሴ እየተደረገ ያለውም በዚህ መልኩ ነው። በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር በአማራ ክልል ወደ 45 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶችን፤ በአፋር ክልል ደግሞ አምስት ትምህርት ቤቶችን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለመገንባት ተነስቷል። ለዚህ ደግሞ ሀብት የማፈላለግ ሥራ ተሰርቷል። በተለይ አሁን ያለው የገበያ ንረት ጉዳይ ትምህርት ቤቶቹን በሚፈለገው ጊዜ ገንብቶ ወደ ሥራ ለማስገባት እጅግ ፈታኝ ነውና ማገዝ ያለበትን ሁሉ አካል በመጠየቅ ለሥራው መፋጠን ይተጋል።

በእገዛው እስከ አሁን በርካታ አካላት እየተሳተፉ ነው። ለአብነት በዲዛይን ሥራው በዋናነት እስካሁን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን እየሰራ ያለው የኢትዮጵያ አርቲስቶች ማህበር ነው። ሥራው በዲያስፖራዎች ጭምር እየታገዘ የሚሰራም ነው። ለዚህም እንደ ማሳያነት የሚነሳው በአፋርና በአማራ ክልል ትምህርትቤት ለመገንባት ከሚንቀሳቀሱት ውስጥ የዲያስፖራ ትረስት ፈንድ አንዱ ነው። ሜንሺንፎርሜሽን የተሰኘ ድርጅትም እንዲሁ በርካታ ትምህርትቤቶችን ለመስራት ቃል ገብቶ ወደሥራ እየገባ ነው። የልማት አጋሮቻችንም እንዲሁ እንገነባለን ያሉበት ሁኔታ አለ። ስለዚህም ትምህርት ሚኒስቴር እየመራው በመጪው 2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን የመማር ማስተማር ሥራው 50 ትምህርት ቤቶች ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ይሆናሉ።

ትምህርት ቤቶቹ የተጀመሩ እንዳሉ ሁሉ ያልተጀመሩትን ወደ ሥራ ለማስገባት ደግሞ መንግስት የተጫራች ልየታ አድርጓል። በቅርቡም ግንባታው የሚጀመር ይሆናል። ለተግባራዊነቱ የዓለም ባንክን ጨምሮ የተለያዩ አካላት ይሳተፋሉ። በዚህም የመንግስት ሀብት ተደምሮበት በተከታታይ ዓመት ውስጥ 150 ትምህርት ቤቶች ይገነባሉ ተብሎ ታስቧል። እስከዚያ ግን ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ሰላም በሰፈነባቸው አካባቢዎች የተለያዩ የአማራጭ መንገዶች አገልግሎት ላይ እየዋሉ ነው። አንዱ የዳስና የድንኳን ትምህርት ቤቶችን መጠቀም ሲሆን፤ ሌላው የትምህርት ቤት ግብዓቶችን በማሟላት በጣም ያልባሰባቸውን ክፍሎች አነስተኛ ጥገና በማድረግ ትምህርት የሚጀመርበትን መንገድ ማስተካከል ነው። በዚህ ደግሞ ብዙዎቹ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- የሀብት ማሰባሰቡ ሁኔታ ምን ይመስላል፤ ምንስ ያህል ያራምደናል ብላችሁ ታምናላችሁ?**

**አቶ ዳዊት፡-** የሀብት ማሰባሰቡ ሁኔታ የጠበቅነውን ያህል አይደለም። ቃል የተገባውና እየተተገበረ ያለው ነገር አራንባና ቆቦ ነው። በዚያ ላይ ከዋጋ ንረቱ አንጻርና ከተሰበሰበው አኳያ እጃችን ላይ ያለው ገንዘብ ሊያስገነባን የሚችለው 50 ትምህርት ቤት ብቻ ነው። እናም ከ1ሺ300 በላይ ትምህርት ቤት ፈርሰው ሩቡን ያህል እንኳን መገንባት ያልተቻለው እንደአገር የመጣው ተደራራቢ ችግር ነው። እናም በጊዜ ሂደት ይፈታል በሚል ለጊዜው ባለ ነገር ለመጠቀም ወስነናል።

**አዲስ ዘመን፡- እስከ አሁን የትምህርት ጉዳይ ካልተነሳባቸው መካከል የትግራይ ክልል አንዱ ነው። ከስምምነቱ በኋላ በዘርፉ ምን ለመስራት ታስቧል፤ ያለው ሁኔታ ምን ይመስልስ?**

**አቶ ዳዊት፡-** አዎ! በክልሉ ያለውን ውስብስብ ችግር ለመፍታት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ የተካሄደው የሰላም ስምምነቱ መልካም አጋጣሚዎችን የፈጠረ ነው። ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመውም በርካታ ሚኒስቴር መስሪያቤቶች ወደስራ ገብተዋል። በተለይም ከመሰረተ ልማት አንጻር ብዙ ነገሮች እየተከናወኑ ናቸው። ቴሌ፣ መብራት፣ ውሃና ጤና በሥፋት እየተከናወኑ ካሉት ውስጥ ይጠቀሳሉ። ይህ ደግሞ የትምህርቱን ዘርፍ ሥራ በእጅጉ ያግዘዋል። በተመቻቸ ነገር ላይ ሥራውን ለማከናወንም ያስችለዋል። ምክንያቱም ትምህርት መብራት፣ ውሃ፣ መንገድ ጨምሮ ሌሎች መሰረተ ልማቶች ያስፈልጉታል። እነዚህ ቀድመው መሟላታቸው ጥሩ መደላደልን ይፈጥራል።

ከዚህ ቀደም የነበሩትን ተሞክሮዎች በማካተት ትምህርት ሚኒስቴር በትግራይ ያለውን ችግር ለመፍታት አስቧል። ትግራይ ላይ ከሁለት ዓመት በፊት ትምህርት ለማስጀመር ብዙ ሥራዎች ተሰርተው ነበርና የሚጎሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ መገመት ይቻላል። በተመሳሳይ የአፋርና የአማራ ክልል የትምህርት ዘርፉ ጉዳት በሚገባ የታየ ስለነበር በዚህ መነሻነት ለመሥራትም ጥሩ እይታን የሚያጎናጽፈን ነው። እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የወደሙ ትምህርት ቤቶችን ዳግም ወደ ሥራ ለማስገባት የአምስት ወር ዕቅድ ተይዟል። በዚህም የሚሰራው ሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ተቋርጦ የነበረውን የመማር ማስተማር ሂደት በቀጣዮቹ አምስት ወራት ሙሉ ለሙሉ ያስጀምራል ተብሎ ይታመናል።

እንደ አገር ጦርነት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የትምህርት መቋረጥ ችግር ታይቷል። ሆኖም እንደ ትግራይ ክልል ግን አይሆንም። ምክንያቱም በሌሎቹ አካባቢዎች ላይ ገባ ወጣ እንጂ ላለፉት ሁለት ዓመታት ትምህርት አልተቋረጠም። በዚህም ችግሮቻቸው ጭምር እንዲለያይ አድርጓል። እንዴት ቢባል በትግራይ ክልል ሙሉ ለሙሉ የትምህርት መዋቅሩ ፈርሷል። መረጃዎችን እንኳን ለመለዋወጥ አስቸጋሪ ነበር። ሆኖም የትምህርት ሥራ የሚቋረጥ አይደለምና ዕቅዱን አቅዶ ወደ ሥራ ለመግባት መነሻ ሀሳብ ከየትም ብሎ ማግኘት ያስፈልጋል። በመሆኑም ከዘርፉ ጋር የሚሰሩ አካላትን በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል።

መረጃዎቹ የትምህርት ሥራውን ለማስጀመር የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉና በሚቀጥሉት አምስት ወራት ምንምን ተግባራት መከወን እንዳለባቸው የሚጠቁሙ ናቸው። ስለሆነም በክልሉ መጀመሪያ ለመስራት የታሰበው የትምህርት ቢሮዎችን ማደራጀትና የሰው ሀብታቸውን ማሟላት ነው። ይህ ከተከናወነ በኋላ በእነርሱ መረጃ ሰጪነት ትምህርት ቤቶችን የመጠገንና ግብዓት የማሟላት ተግባር ይከናወናል።

በጦርነቱ ምክንያት የወደሙትንና እድሳት የሚደረግላቸውን በመለየት በመረጃው መሰረት ለመማር ማስተማሩ ምቹ ይደረጋል። ቀጣዩ ሥራ የሚሆነው የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ግብዓት አቅርቦት ነው። ምክንያቱም በክልሉ መጻሐፍትና መሰል ግብዓቶች ያስፈልጋሉ። በዚህም ቅድሚያ የሥርዓተ ትምህርት ክለሳው ይደረግና ተማሪዎች በጦርነቱ ምክንያት መማር ባለመቻላቸው የመጡ በርካታ ችግሮችን እንፈታለን። ያሉበትን ክፍል በደንብ አውቀውት ወደቀጣዩ ክፍል እንዲዛወሩ እናስችላለን። ከዚያ በመቀጠል እንደ አገር የወረደውና ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ግንዛቤ የመፍጠር ተግባር ይከናወናል። በዚያው ልክ መጽሐፍትን ማዘጋጀትና አባዝቶ የማቅረብ ተግባር ይከናወናል።

ክልሉ ላይ የመማር ማስተማር ሥራው ሲጀመር ከሌሎች ክልሎች በተለየ መልኩ ይሆናልም። ምክንያቱም መጀመሪያ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን እንዲሁም ወላጆች በስነልቦና መታከም አለባቸው። ከነበሩበት የስነልቦና ጭንቀትም መላቀቅ አለባቸው። እናም በአብዛኛው ትምህርቱን በማስጀመር ሂደት ውስጥ የሚከናወነው አዕምሮን በማነቃቃት ነው። ወላጆች ጭምር ትምህርት ቤት መጥተው ከልጆቻቸው ጋር አዕምሯቸውን እንዲያሳርፉ ይደረጋል። ከትምህርት ቅበላው ጀምሮ የቀደመውን ድባብ የመቀየር ተግባር ይከናወናል።

አሁን ባለው ሁኔታ በክልሉ የሚኖሩ ወላጆች ልጆቻቸውን ቀርቶ ራሳቸውን መግበው የሚያድሩ አይደለም። ትምህርት ደግሞ ተመግቦ መምጣትን ይጠይቃል። ስለዚህም በምግብ እንዳያስቡ ለማድረግ በአፋርና በአማራ በመጠኑም ቢሆን እየተደረገ ያለው የተማሪዎች ምገባ ስራ በትግራይ ክልልም እንዲጀመር ይሰራል። ነገር ግን በዚህ ላይ ብዙዎች መረባረብ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም መንግስት አሁን ላይ ብዙ ወጪ አለበት። እናም የተማሪዎችን ምገባ ለማስጀመር አጋር አካላት፣ በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ጦርነቱ ያልደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ ዜጎች ሊያግዙ ይገባል።

ትምህርት ከምንም በላይ የሰላም ድባብን ይፈልጋል። ያ እስኪመጣ ድረስ የምንሰራው ሥራ ዕቅድ ቢጠናቀቅም መጠበቁ ግድ ነው። ግቡ ተብሎ ሲፈቀድ ለአምስት ወር የተያዘውን ዕቅድ ወደ መተግበሩ ይገባል። በተከታታይ ታስበው የተቀመጡትም የሚተገበሩ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የተለያዩ ችግሮች በአገር ደረጃ ሲከሰቱ መልካም አጋጣሚዎችን ጭምር ይዘው እንደሚመጡ ይታሰባል። ለዘርፉ ችግሩ እንዳለ ሆኖ ምን ምን መልካም አጋጣሚዎች መጥተዋል ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ዳዊት፡-** ልክ ነው። ችግር ብቻ ማየት ከስህተት አይመልስም። መልካም አጋጣሚዎችን መጠቀምም እንጂ። እናም በአገር ደረጃ የነበሩት ችግሮች ብዙ ነገሮች አስተምረውናል። ከቅርቡ ብንነሳ እንኳን ኮሮና ብዙ መልካም ትምህርቶችን ለዘርፉ ሰጥቷል። የመጀመሪያው በጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ቤትን ለመገንባት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ምክንያቱም ተማሪዎች በቤታቸው በመሆናቸው እንደልብ መስራት አስችሏል። ሕብረተሰቡ ወደ ልቡ ተመልሶ ስለነበር በጎ ማድረግ ላይ ሁሉም እንዲረባረብ አድርጓል። በተለይም በመልሶ መገንባቱ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ እጅግ የሚገርም ነበር።

ስምምነቱ በራሱ መልካም አጋጣሚ ነው። ምክንያቱም ትምህርት ላይ የማይገባ የማህበረሰብ ክፍል የለም። እናም ሰው ወደልቦናው ተመለሰና ተረጋጋ ማለት መማር ማስተማሩ ሲጀመር ጥሩ ድባብ ይፈጠራል። ደስተኛ የሆነ ዜጋን እንደማስተማር ደግሞ ስኬታማ የሚያደርግ ነገር አይኖርም። ስለሆነም ሰላምና መረጋጋቱ አሁን ባለበት ሁኔታ ከቀጠለ መማር ማስተማሩን በጥሩ ሁኔታ ማስኬድ ይቻላልና መስማማቱ መልካም አጋጣሚ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደአጠቃላይ ከዘርፉ ጋር በተያያዘ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካልዎት ቢናገሩ?**

**አቶ ዳዊት፡-** ሁለት ነገሮችን በዋናነት ማንሳት እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከዚህ በበለጠ ሊጠናከር ይገባል የሚለው ነው። ምክንያቱም በግጭቱ አካባቢ ያሉ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ለመምጣት መሰረታዊ የሆነ ነገር ያስፈልጋቸዋል። ይህም ምግብ ነው። ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን በአፋርና አማራ ክልል በተወሰነ ደረጃ ቢጀምረውም በቂ አይደለም። ትግራይ ላይ ያለው ሁኔታ ደግሞ እጅግ ከባድ ነው። ስለዚህም ማህበረሰቡ መንግስትን በትምህርት ቤት ምገባ ሊያግዘው ይገባል።

ሁለተኛው ማህበረሰቡ የሚያደርገውን ድጋፍ መናቅ የለበትም የሚለው ሲሆን፤ ብዙ ለተጎዳ ትንሿ ትልቅ ናት። እናም ደብተርና እስኪርብቶን ጨምሮ የትምህርት መሣርያዎችን ማገዝ ላይም መረባረብ ይኖርበታል። ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያን የሚወዱ ሁሉ በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ መደጋገፍ ይኖርባቸዋል ማለት እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ ዳዊት፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ‹‹የአገሪቱ የሰላም ሁኔታ እንዳይዋዥቅ ብዙ መሠራት አለበት››

## አንጋፋው ፖለቲከኛ ዶክተር አረጋዊ በርሄ

ምህረት ሞገስ

መንግስት የሰሜኑ ጦርነት እንዳይነሳ እና ከተነሳም በኋላ በተደጋጋሚ ጦርነቱ ቆሞ ሰላም እንዲሰፍን ስምኗል፤ አስስምኗል። “ ክብር ከኢትዮጵያ ሰላም አይበልጥም “ ብሎ የሰነዘረው የሰላም ጥሪ ሳይሳካ በሶስት ዙር ጦርነት ተካሂዷል። ያም ሆኖ አሁን በመንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን አድርጓል።

የሰላም ስምምነቱን መርህ ተከትሎ በትግራይ ክልል ሰብዓዊ እርዳታ ያለ ገደብ እንዲገባ ተደርጓል። መድሀኒት፣ የነዳጅ አቅርቦት፣ ገንዘብ የመሳሰሉ ወሳኝ ድጋፎች ወደ በብዛት ወደ ክልሉ ገብቷል። ተቋርጠው የነበሩ የመሰረተ ልማቶችን በመጠገን ወደ ስራ እንዲገቡ ሆነዋል። በትግራይ ክልል የተጀመረው አገልግሎት የማቅረብ ሥራ እንዲፋጠን ከመስራት በተጨማሪ፤ የሰላም ስምምነቱን ወደመሬት ለማውረድ ጭምር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የተመራ የፌዴራል መንግሥት የልዑካን ቡድን በመቀሌ ተገኝቶ ከሕወሓት አመራሮች ጋር የተለያዩ ውይይቶችን አድርገዋል።

በትግራይ ክልል በጦርነቱ ምክንያት ከቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙ ዜጎች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽ የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን እና በክልሉ የውሃ ማጣሪያ ጣቢያዎች ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ እየተሰራ መሆኑም ታውቋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ መቀለ የሚያደርገውን በረራ ከመጀመር አልፎ በቀን ሁለት ጊዜ በረራውን ማካሄዱን ቀጥሏል። የኢትዮ ቴሌኮም አገልግሎትም በክልሉ በተለያዩ ከተሞች እንደገና አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። በጦርነቱ ጉዳት የደረሰበት 931 ኪሎ ሜትር የቴሌኮም ፋይበር ኦፕቲክስ እንደተጠገነ እና በ870 ኪሎ ሜትር ፋይበር ኦፕቲክስ ገና ጥገና እየተከናወነ መሆኑን ታውቋል። ይህ ሁሉ ሲቃኝ የሰላም ስምምነቱ መሰረት መያዙን እና ችግሩም እየተቃለለ መምጣቱን የሚያመለክት ነው።

የሰላም ስምምነቱ ለአገር ሰላም በተለይም ለትግራይ ክልልና ህዝብ የሚኖረው አጠቃላይ አንደምታ፣ የሰላም ስምምነቱ ዘላቂ የሚሆንበትን መንገድ እና መንግስትም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ሊቀበለው ይገባል፤ ምንስ መደረግ አለበት? ስንል አንጋፋውን ፖለቲከኛ ዶክተር አረጋዊ በርሄን ጠይቀን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል። መልካም ንባብ፡-


ፎቶ፡-ገባቦ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡-የሰላም ስምምነቱን እንዴት አዩት ከሚለው እንጀምር?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** አገራችን ኢትዮጵያ በጦርነት በግጭት ስትታመስ ቆይታለች። ይሔ ጦርነት በህዝቡ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ዓዕምሯዊ ጫናም ሲፈጥር ከርሟል። ይህ ለሁለት ዓመታት በከፋ መልኩ ሲፈጠር የነበረው ጫና መቋጨቱ ጤነኛ ዓዕምሮ ያለው ሰው በደስታ ሊቀበለው ይገባል የሚል እምነት አለኝ።

በእውነቱ በእኛ በኩል የተቀበልነው በደስታ ነው። ሕዝቡም ደስ ተሰኝቷል። ምክንያቱም እፎይታን አግኝተናል። ከሰላም ስምምነቱ ቀጥሎ አሁን እየታዩ ያሉ ሁኔታዎች በአብዛኛው የሚበረታቱ ናቸው። አንዳንድ ቀዳዳዎች ሊኖሩ ቢችሉም ብዙ ነገር ጥሩ ነው። ሕዝቡም ስምምነቱን በሙሉ ልቡ ተቀብሎ ደግፏል። ስለዚህ ደስተኞች ነን።

**አዲስ ዘመን፡- በመንግስት በኩል ከጦርነቱ በፊትም ሆነ ከጦርነቱ በኋላ ለሰላም የታየውን ቁርጠኝነት እንዴት ይገመግሙታል?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** መንግስት በእውነቱ ለሰላም ያደረገው ጥረት እጅግ የሚመሰገን ነው። ችግሮች በጦርነት የተፈቱ ቢመስሉም ጦርነት ዘላቂ መፍትሔ አይሆንም። ዋናው ነገር ነቅቶ በሰላም እና በምክንያታዊ ድርድር ችግር ሲፈታ ሁሉም የሚቀበለው ዘላቂ መፍትሔ ይገኛል። በጦርነት ከሆነ ግን አንዱ አሸናፊ ሌላው ተሸናፊ ይሆንና ተሸናፊው ቂሙን ለመወጣት ጊዜ ይጠብቃል፤ አሸናፊው ደግሞ እንደገና እንዳይነሳበት ክትትል ያደርጋል። የአይጥ እና የድመት ሽኩቻ ይሆናል። ስለዚህ መንግስት ችግሩ በሰላም እንዲፈታ ያደረገው ተደጋጋሚ ጥረት የሚመሰገን ነው። ይሔ መሰረታዊ ሃሳብ ነው። ይህን ስል የመንግስት ተቀዳሚ ሥራ ሰላም እና መረጋጋትን መፍጠር መሆኑ መረሳት የለበትም።

መንግስት በአገሪቱ ህግ ተከብሮ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ዋነኛ ሥራው ነው። ስለዚህ ይህን ለማድረግ ሕገመንግስቱ ኃላፊነት ጥሎበታል፤ ደግሞም ህጉ ያስገድደዋል። እርምጃ መውሰድም ይችላል። ፖሊስ፣ ጦር ሰራዊት እና መከላከያ ኃይል አስፈላጊ የሚሆኑት ለዚህ ነው። ይህን የሰላም መንገድ የማይከተሉ አፍራሽ የሆኑ ፅንፈኝነት የሚያጠቃቸው ወገኖችን ደግሞ መቆጣጠር ግዴታ ነው። ችግሮችን ለመፍታት የሰላም መስመርን መምረጥ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም መንግስት መወጣት ያለበትንም ኃላፊነት መወጣት ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች መቀሌ ገብተው ውይይት አካሂደዋል። ይህንን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** ከአፈ-ጉባኤው ታገሰ ጫፎ ጀምሮ የተለያዩ ሚኒስትሮች እና የሥራ ኃላፊዎች ወደ ትግራይ ሄደዋል። በጦርነቱ ምክንያት ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎቶች ሥራ እንዲጀምሩ እና መሰረተ ልማቶችም እንዲሟሉ እየሠሩ ነው። ሁሉም እንደሰማው እና እንዳየው አየር መንገዱ ሥራ ጀምሯል። የአየር ትራንስፖርት ክፍት ሆኗል። በተጨማሪ የቴሌ፣ የባንኮች፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎች ስራ ጀምረዋል። የትምህርት አገልግሎቶች መጀመር አለባቸው። ሕዝቡ ትርጉም ያለው ህይወት እንዲመራ ሊደረግ ይገባል። የስምምነት ውሉን ተከትሎ የስራ ኃላፊዎቹ መላካቸውም ሆነ ሥራ መጀመሩ ተገቢ ነው። በቀጣይም መጠናከር አለበት ብዬ አምናለሁ።

የአገራችን የሰሜኑ ክፍል ከጥንት ከግብፅ ወረራ ጀምሮ የጦርነት ቀጠና ነው። ከጣሊያን ጋርም ጦርነት የተካሔደበት አካባቢ ነው። ከዛም በኋላ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የፀረ ደርግ ታጣቂዎች ሲዋጉበት የነበረ ነው። በዚህ ምክንያት አካባቢው አጠቃላይ ኢኮኖሚው ደቋል። ቆይቶ የማንሰራራት ዕድል ቢያገኝም በተለያየ መልኩ በሙስና እና በማይረባ አካሄድ ፈራርሷል። ሕዝቡ ዘመኑን ሲማረር፣ ሲራብ እና ሲሰቃይ ኖሯል። በዛ ላይ የአሁኑ ጦርነት ሲጨመርበት ልጆቹን የሚያጣበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በተጨማሪ ኑሮውን መምራት የማይችልበት ከባድ ችግር አጋጥሞታል። ስለዚህ የመንግስት ባለስልጣኖች በዚህ ደረጃ ወስነው መሄዳቸው ተገቢ ነው። ነገር ግን ከዚህም በላይ መቀጠል እንዳለባቸው ለማሳሰብ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥም እርሶ እንደገለፁት አካባቢው የተጎዳ ነው። ከትግራይ በተጨማሪ ሌሎችም አካባቢዎች ተጎድተዋል። ከዚህ አንፃር በዚህ ጊዜ ሰላም አሁን በተያዘው መጠን ምን ያህል አስፈላጊ ነው?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** እንደተነሳው በዚህ ጦርነት የተጎዳው የትግራይ አካባቢ ብቻ አይደለም። በቅድሚያ የአማራ እና የአፋር ክልል ህዝቦች ተጎድተዋል። ምክንያቱም የጦርነቱ ወላፈን ወደ እነርሱም ሲሻገር ነበር። ከዚህ በላይም ወደ ሌሎች አካባቢዎች ወደ ወለጋም ሆነ ወደ ቤኒሻንጉል እንዲሁም አንዳንድ የኦሮሚያ ክፍሎች ከጦርነቱ ጋር ንክኪ ያላቸው ድርጅቶች የፈጠሩት ችግር በህዝቡ ላይ ከባድ መከራ አምጥቷል። ስለዚህ ይህንን ነገር በቅጡ መያዝ አስፈላጊ ነው። መንግስት ይሄ ገብቶታል ብዬ አስባለሁ። የሰላም ስምምነት እኔ እንደሚገባኝ በጦርነት ገፍቶ ሄዶ እንገነጠላለን የሚሉ አመራሮች በጦርነት መቀጠል እንደማይችሉ አረጋግጠላቸዋል። እነርሱም ኢትዮጵያ አንድ እንደሆነች ልዓላዊ አገር እንደሆነች፣ ሕዝቡም ተባብሮ እንደሚገዳደራቸው ሰራዊቱም በሙሉ ልብ እንደሚዋጋቸው ሲያዩ እንደማይሆንላቸው ሲያረጋግጡ ወደ ሰላም መጥተዋል። ስለዚህ ይህ አካሄድ በሌሎቹ አፈንጋጮች እና ፅንፈኞች ላይም ሊሰራ የሚችል ይመስለኛል። በእርግጥ ይህንን ፈለግ መከተሉ ወደ ሰላም እንዲመጡ ለማድረግ ነው። ጥሩ መንገድ ነው። በጦርነት የሚመጣ መፍትሔ ተመራጭ አይደለም።


**አዲስ ዘመን፡- ሰላም መስፈኑ ለትግራይም ሆነ ለአማራ ህዝብ እንዲሁም ለአፋር በአጠቃላይ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነው?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** ከአጠቃላይ ከሕዝቡ አንፃር ሰላም የመስፈኑን ጉዳይ ስናየው ትልቅ አንድምታ አለው። ሁሉም ሰው ሲሰቃይ ነበር። ሰላም መምጣቱ ለህዝቡ የተረጋጋ ኑሮ እጅግ አስፈላጊ ነው። በጦርነት የሚገኝ ትርፍ የለም። ሞት፣ የአካል መጉደል፣ የንብረት መውደም እንጂ ሌላ ትርፍ የለውም። ጊዜያዊ አሸናፊነት ቢኖርም እነዚህን ትልልቅ መስዋዕትነቶች ተከፍለው ነው። ስለዚህ ይህ ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎም የሚመጣው ለውጥ ጠቃሚ አይደለም። በተካሄደው ጦርነት ቢያንስ ከ500 ሺህ ያላነሰ ሰው ሞቷል። ብዙ ሰው የአካል ጉዳተኛ ሆኗል። ብዙ ሰው ደግሞ ተፈናቅሏል። የጦርነት ውጤት ይሔ ነው። ስለዚህ ይህንን መለስ ብሎ ማየት እና ከእንግዲህ ወዲህ ጦርነት አስፈላጊ አይደለም። የሚያስፈልገው ሰላም ብቻ ነው ብለው ቆርጠው መመለስ አለባቸው።

በእርግጥም በጦርነቱ ተጠቃሚዎች ይኖራሉ፤ በኮንትሮባንድ እና በተለያየ ማጭበርበር በሙስና ‹‹ግርግር ለሌባ ይመቻል›› አንዳንዶች እንደሚባለው የሰላሙን ሂደት ለማሰናከል መሞከራቸው አይቀርም። በተለያየ ምክንያት አንዳንድ ያፈነገጡ ካሉ ተስፋ የላቸውም። ምክንያቱም ህዝቡ በፍፁም ጦርነት መሮታል። እንዲህ ዓይነቶቹን ጭራሽ አይፈልጋቸውም። ሕዝቡ ገና አልተደራጀም እንጂ አንዳንድ ምልክቶችን እያሳየ ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ጠመንጃ አንግቶ እየዞሩ ማስገደድን አንቀበልም እያለ ነው። መንግስትም ቆርጦ ተነስቷል። የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቆርጠው ተነስተዋል። ሁላችንም ለሰላም ቆርጠን ተነስተናል። ስለዚህ በሁሉም አካባቢ ሲታይ ሊኖሩ የሚችሉ እንቅፋቶች ለጊዜው ብቅ ብቅ ሊሉ ይችላሉ። ነገር ግን ከዚህ በኋላ ጦርነት ፈላጊዎች መጨረሻቸው ተስፋ የሌለው ጨለማ እና ወዳቂ በመሆኑ ለውጡ ሥር እየሰደደ ሊሄድ እንደሚችል እና እንደሚሳካ እርግጠኛ ነኝ።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ



**አዲስ ዘመን፡- መንግስት ቀድሞም ቢሆን ጦርነት እንዳይመጣ ሽማግሌዎችን ልኳል፤ በተደጋጋሚ የሠላም ጥሪ አቅርቧል። አሁንም ስስምምነቱ መተግበር እየሰራ፣ ቀደም ሲል ከሳይ እንዳነሳነው በትግራይ ክልል መሰረተ ልማቱን ስማሟላት ጥረት እያደረገ ነው። ከዚህ በኋላስ ምን ማድረግ አስበት ይላሉ?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** *መንግስት ማድረግ ያለበትን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። አንደኛ መንግስታዊ ግዴታውን መወጣት እና ህግ ማስከበር አለበት። ሕገመንግስቱ ያስቀመጠውን ግዴታ ማለትም ሰላም ማስፈንን በተመለከተ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት። በቅድሚያ መንግስት የሚቋቋምበት ዋነኛው ምክንያት ሰላም እንዲያሰፍን ነው። ሥርዓት እንዲኖር ሕግ እንዲከበር ነው። ሌሎቹ ነገሮች ማለትም ግንባታም ሆነ ሌሎች መሰረተ ልማቶች የሚመጡት ከሰላም በኋላ ነው። ስለዚህ መንግስት በቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ በሙሉ ኃይሉ በመንቀሳቀስ ሰላምን ማረጋገጥ ይገባዋል። የአገሪቱ የሰላም ሁኔታ እንዳይዋዥቅ ብዙ መሥራት አለበት። ሰላም ማስፈን የመንግስት ግዴታ ነው። በትግራይ ይሔ ባለመሆኑ በጊዜያዊ አስተዳደሩ ወቅት ብዙ ዋጋ ከፍለናል። አንዱ ይሔ ነው።*

ሌላው ከላይ እንደገለፅኩት አካባቢው በጦርነት የተጎሳቆለ ነው። የነበሩት አመራሮች ደግሞ ጥሩ ስላልነበሩ ይባስ ነገሩ ሁሉ ተበላሽቶ ወደ ጦርነት ተገባ። በእያንዳንዱ ጎጆ የቤተሰቡ አባል ያልሞተበት የለም። የሞተው እንኳን ይቀበራል። ዓይኑ የጠፋ፣ እግሩ የተቆረጠ፣ እጁ የተቆረጠ እና አካል የጎደለው ብዙ ነው። ይሔ ሁሉ ወደ የቤቱ ይገባል። ያንን ሁሉ መከራ ሲሸከም የነበረው ሕዝብ ተጨማሪ መከራ ይደርስበታል። መንግስት ይህንን ሁሉ ተገንዝቦ የአካባቢውን ኢኮኖሚ መደገፍ፤ መሰረተ ልማቱን ማሟላት እና የሥራ ዕድል መፍጠር ይኖርበታል።

የጤና ተቋማት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ እና ወደ ሶስት ዓመት ትምህርት ያቆሙትን ልጆች ወደ ትምህርት ገበታ ማምጣት ያስፈልጋል። ያለበለዚያ ያልተማረ ልጅ ወደ ስርቆት ወይም የሽምቅ ተዋጊ ጠባቂ ይሆናል። ስለዚህ ወጣቱን ወደ ትምህርት እና ወደ ተለመደ የዕለት ተዕለት ኑሮ ማምጣት የግድ ነው። በዚህ ጊዜ ትልቅ የሥነዓዕምሮ ቀውስ ያጋጥማል። በሙሉ ህብረተሰቡ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሽማግሌዎች ሁሉም የህረተሰብ ክፍል፤ ይህ ሁሉ መከራ የበዛብን ምን በድለን ነው? የሚል ጭንቀት በውስጡ አለ። አንዳንዱ በግልፅ ችግሩ የት እንዳለ አያውቅም። ችግሩ ምን እንደሆነ እና የት እንዳለ አለማወቅ ራሱ የስነዓዕምሮ ቀውስ ያመጣል። ስለዚህ መንግስት ችግሩ ምን እንደነበረ ሕዝቡ እንዲያውቅ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከታች ጀምሮ ወደ ላይ ቅስቀሳ፣ ትምህርት፤ የነፃ ሃሳብ ውይይት እና የመልካም ሃሳብ ልዕልና እንዲኖር መንግስት ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት። ይህ ሲሆን ሕዝቡ ይረጋጋል። ሕዝቡ በነፃነት ሃሳቡን ይገልፃል፤ ይደራጃል፤ የሚፈልገውን ያውቃል፤ ስለዚህ በቀላሉ ተነጋግሮ ችግሮችን መፍታት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ወደፊት መሳው ኢትዮጵያውያን ከሰላም ጋር ተያይዞ ምን ማድረግ አስባቸው?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** ሰላም እንደውሃ ነው። ውሃ በሕይወት ውስጥ የማይገባበት የለም። ውሃ ሙሉ ለሙሉ ከሕይወት ጋር የተቆራኘ ነው። ውሃ ኃይል ነው፤ ውሃ አትክልት ነው፤ ውሃ ምግብ ነው፤ ውሃ ከሌለ ሕይወት የለም። ሰው ብቻ ሳይሆን አትክልትም ሆነ እንስሳት ምንም ነገር ያለውሃ አይኖርም። ሁሉም ይደርቃል፤ ሁሉም ያልቃል፤ ይደቃል። ሰላምም ተመሳሳይ ነው። ሰላም ከሌለ ዕድገት የለም። ሰላም ከሌለ አብሮ መኖር አይታሰብም። ሰላም ከሌለ የሚበላው ቀርቶ የሚቀመስ ይጠፋል። ሰላም ከሌለ የሚኖረው ግጭት ብቻ ነው።

አሁን ብቻ ሳይሆን በፊትም ቢሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የሰላም እጦት ነበር። እውነቱን እንነጋገር ከተባለ በኢህአዴግ ጊዜም ሰላም አልነበረም። እንዲሁ ከላይ ከላይ ሰላም ያለ የሚመስልበት ሁኔታ ነበር፤ ነገር ግን እውነተኛ ሰላም አልነበረም። በጉጂ እና በጌዲኦ፤ በጋምቤላ እና በቤኒሻንጉል፤ በአሪና በኮሞ፤ በሃረር አካባቢም ብቻ እንጥቀስ ከተባለ በየአካባቢው ጦርነት እና ግጭቶች ነበሩ፤ ነገር ግን ሚዲያውን አንድ ድርጅት ብቻ ይቆጣጠረው ስለነበር ግጭቶቹ አይገለፁም እንጂ በፊትም ሰላም አልነበረም። ስለዚህ ህዝቡ ብዙ ተሰቃይቷል። አሁን ያለው ግጭትም የዛ ቅሪት ነው።

አሁን የሚታዩት ግጭቶችም በፊት ከነበሩት ግጭቶች የመነጩ ናቸው። ስለዚህ የሰላም ማጣቱ ሁኔታ ኢትዮጵያን ጎድቷታል። ይሔ የሰላም ማጣት ኢትዮጵያውያንን ድህነት ላይ ጥሎናል። ስለዚህ ከጦርነት መውጣት ግዴታ ነው። ከጦርነት ለመውጣት ደግሞ ሰላም በትክክለኛው መንገድ መረጋገጥ አለበት።

ሰው ግለሰባዊ መብቱም ሆነ የጋርዮሽ መብቱ ከተከበረለት የሚፈልገው በሰላም ሰርቶ መኖር ብቻ ነው። መብት ካልተከበረ ግን በሰላም መኖር አይቻልም። በዚህ ላይ ሁሉም ግንዛቤ ወስዶ ችግር ያለበትም በሰላማዊ መንገድ በውይይት ችግሩን እየፈታ፤ አገርን ሰላም ማድረግ ይቻላል። የሰለጠነ አሰራርም ይኸው ስለሆነ፤ በዚህ መንገድ መቀጠል ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ቀድሞም ቢሆን በኢትዮጵያ ሰላም እንዳይኖር የሚፈልጉ አካላት መኖራቸው ይታወቃል። የሰላም ስምምነቱ እንዲደናቀፍ ከውጪም ሆነ ከውስጥ የሚጥሩ ኃይሎች መኖራቸውም አይካድም። የእነዚህ አላማ ምንድን ነው ብለው ያምናሉ?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** ይሔ ከድሮም ጀምሮ የታወቀ ነው። ከበፊትም አሜሪካን እና አውሮፓዎች እዚህ የደረሱት እና በከፍተኛ መጠን ሃብት ማከማቸት የቻሉት ከቀኝ ግዛት በሰበሰቡት ሃብት ነው። ይሔ ብዝበዛና ዝርፊያ አሁንም እንዲቋረጥ አይፈልጉም። ስለዚህ አፍሪካን በአጠቃላይ ሶስተኛውን ዓለም በተለያየ መልኩ መቆጣጠር ይፈልጋሉ። እዚህ ላይ ራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዳይኖር ይፈልጋሉ።

በአፍሪካ ነፃ ኢኮኖሚ እንዲገነባ አይፈልጉም። ለምሳሌ ለታላቁ ግድብ አንድም ሳንቲም አልረዱም። ነገር ግን ለህፃናት ይህንን እየረዳን ነው፤ ለሴቶች ይህንን አድርገናል፤ ለዚህ ድርጅት ይህን ያህል ወጪ አውጥተናል ይላሉ። ነገር ግን ይሔ ዝም ብሎ ለለማኝ ቁራሽ እንጀራ እንደመስጠት ነው። ለማኙ ያችን ቁራሽ እንጀራ ሁልጊዜ እየለመነ እንዲኖር ማድረግ ነው። ቁራሽ እንጀራን መስጠት መፍትሔ አይሆንም። ለምሳሌ አንድ ሰው ባህርዳር ቆሞ ሲለምን አሳ ከመስጠት ይልቅ አሳ እንዴት ማስገር እንደሚቻል ለማስተማር ፍቃደኝነቱ ካለ ሰውየውን ሙሉ ለሙሉ ከችግሩ ማላቀቅ ወይም እንዳይለምን ማድረግ እና መፍትሔ ማመላከት ይቻላል።

የውጪ ኃይሎች የሚፈልጉት ከልመና አጥር እንዳንወጣ ማድረግ ነው። እነ ብሊንከን እና ሌሎችም እዚህ እየመጡ ሰላም ፍጠሩ ሲሉ ነበር። ነገር ግን ዓላማቸው የሚታዘዛቸው ኃይል ስልጣን እንዲይዝ የማድረግ ፍላጎት ነበራቸው። ይሔ የታወቀ ፖለቲካ ነበር፤ ነገር ግን አልተሳካላቸውም። አሁን ደግሞ የሚያስደስተው የኢትዮጵያ ባለስልጣናትም መቀሌ ድረስ ሔደው ከሕወሓት አመራሮች ጋር ተደራድረው ሰላምን ለማስቀጠል የወሰዱት እርምጃ ለእነርሱ የሚቆረቁር መልዕክት ነው። ችግራችንን በራሳችን መፍታት እንደምንችል የሚያሳይ ነው። እናም ቢለቁን ጥሩ ነበር።

በሌላ በኩል የእነርሱ ተቀጣሪዎች የውስጥ አርበኞች አሉ። የእነርሱን ፍርፋሪ እየለቃቀሙ በዚህ እንወጣለን፤ በዚህ እንገባለን፤ ይህን እንሰራለን ይህንን ለውጥ እናመጣለን የሚሉ አሉ። እነርሱን ማጋለጥ ይገባል። በተለይ የነፃ ሃሳብ ውይይት ከዳበረ እነርሱን ማጋለጥ ይቻላል። ለምን ይህን እንደሚያደርጉ ማጋለጥ ይቻላል። በዚህ ላይ ጋዜጠኞች ከፍተኛውን ሚና መጫወት ይችላሉ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት ሙሰኞችን አጋልጡ፤ መጠየቅ ያለበትን ጠይቁ ብለዋል። ስልጣኑ ተሰጥቷል፤ ስለዚህ ጋዜጠኞች ያለፍርሃት ግፊት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን መንግስት እና ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ምን ማድረግ አስባቸው ይላሉ ?**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** የእኛ አገር የፖለቲካ ኃይሎች ከኢህአዴግ ጋር የተቆራኙ ናቸው። በአብዛኛው ኢህአዴግ የፈጠራቸው ናቸው። እኔ እንዳየኋቸው የራሳቸው ወጥ አመለካከት አይዶሎጂ ያላቸው አይመስለኝም። በተለያዩ ውይይቶች ላይ አይቻቸዋለሁ። የጋራ ምክር ቤቱ ላይም ስሳተፍ ነበር። ወጥ የሆነ ሃሳብ፣ ወጥ የሆነ ዓይዶሎጂ ወይም የፖለቲካ ፕሮግራም፣ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ፖሊሲ የላቸውም። አንዳንዶቹ ምርጫ ቦርድ የሚሰጣቸውን የሥራ ማካሄጃ ብር ለመለቃቀም ሲሽከረከሩ ይውላሉ። ስለዚህ ይሔንን ለመፍታት ምናልባት ምርጫ ቦርድ መልዕክቱ ቢደርሰው መልካም ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች ትክክለኛ አቋማቸውን አይዶለጂካልም ሆነ ፖለቲካል አቋማቸውን መድረክ ላይ እየወጡ እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር እየተፎካከሩ ጠርተው እንዲወጡ መደረግ አለበት። ምርጫ ቦርድ ተመሳሳይ ሃሳብ ካላቸው ጋር እንዲጣመሩ ማድረግ አለበት። 50 እና 60 ፓርቲ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም አያደርግለትም። ሲያወሩ የሚውሉትም ስለመከፋፈል ነው። ስለዚህ ምርጫ ቦርድ ትልቅ ኃላፊነት አለበት።

ሁለተኛ በሰላሙ ሂደት ላይ ደግሞ የሚነቀፍ ነገር የለም። የሰላም ስምምነቱን ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አልነቀፉትም እየደገፉት ነው። ነገር ግን ጠንካራ ድርጅቶች ስላልሆኑ ጠንካራ ውጤት ማምጣት አልቻሉም። ቢሆንም መረሳት የሌለበት ፍላጎቱ አላቸው። በእርግጥ ግማሾቹ የሕወሓት ደጋፊዎች እንደነበሩ እናውቃለን። ነገር ግን አሁን ድጋፋቸውን አቁመው ሰላም መሰረት እንዲይዝ እንዲያደርጉ መምከር እንፈልጋለን። በተረፈ ግን ይህች አገር ማደግ የምትችለውና ከጉስቁልና ኑሮ የምትወጣው ሰላም ሲሰፍን ብቻ ነው። በሰላማዊ መንገድ መወያየት ስንችል፤ ስንደራደር እና ስንከራከር ነው። የሚያዋጣው ነገር ህዝብ ፊት ቀርበን ህዝቡ እንዲደግፈን ስናደርግ ብቻ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስስነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናስሁ።**

**ዶክተር አረጋዊ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

**‹‹ከዚህ በኋላ ጦርነት ፈላጊዎች መጨረሻቸው ተስፋ የሌለው ጨለማ እና ወዳቂ በመሆኑ ስውጡ ሥር እየሰደደ ሲሄድ እንደሚችል እና እንደሚሳካ እርግጠኛ ነኝ። ››**

# ዓለም አቀፍ

## እስራኤል በኃይል የያዘቻቸው የፍልስጤም ግዛቶችን በተመለከተ አስተያየት እንድትሰጥ ተጠየቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ እስራኤል በኃይል የያዘቻቸው የፍልስጤም ግዛቶች በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሕግ አስተያየት እንዲሰጥ ጠየቀ። የሕግ አስተያየቱ እንዲጠየቅ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በ87 አገራት የተደገፈ ሲሆን ዩናይትድ ኪንግደም እና አሜሪካን ጨምሮ 26 አገሮች ደግሞ ተቃውመውታል።

የድምጽ አሰጣጥ ቤንጃሚን ኔታንያሁ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ቃለ መሐላ ከፈጸሙ ከአንድ ቀን በኋላ የተካሄደ ነው።

እስራኤል ከጋዛ ብትወጣም አሁንም ዌስት ባንክን ተቆጣጥራለች። የተባበሩት መንግሥታት አካባቢውን በኃይል እንደተቆጣጠረች ነው የሚመለከተው።

እስራኤል መላዋ እየሩሳሌምን ዋና ከተማዋ እንደሆነች ትገልጻለች። ፍልስጤማውያን ደግሞ ምሥራቅ እየሩሳሌምን የወደፊቷ የፍልስጤም መንግሥት ዋና ከተማ ነች ይላሉ። ዩናይትድ ስቴትስ ከተማዋ የእስራኤል ዋና ከተማ እንደሆነች ዕውቅና ከሰጡ ጥቂት አገሮች አንዷ ነች።

ፍልስጤማውያን ዌስት ባንክ፣ በእስራኤል በኃይል የተወሰደችው ምሥራቃዊ እየሩሳሌም እና የጋዛ ሰርጥ የወደፊቷ የአገራችን አካል ናቸው ይላሉ።

የፍልስጤም ባለስልጣናት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን የውሳኔ ሃሳብ ድል ነው ሲሉ አወድሰዋል። እስራኤል "በሕዝባችን ላይ ለምትፈጽመው ወንጀል ተጠያቂ የምትሆንበት ጊዜ አሁን ነው" ሲሉ ነቢል አቡ ሩዲነህ ተናግረዋል። አዲሱ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር በበኩላቸው ውሳኔው "የተዋረደ" ሲሉ ገልጸውታል።

ኔታንያሁ ቅዳሜ ማምሻውን እንደተናገሩት "የአይሁድ ሕዝብ በገዛ መሬታቸው ላይ ወራሪዎች አይደሉም። ዘላለማዊ በሆነችው ዋና ከተማችን እየሩሳሌምም ወራሪዎች አይደሉም። የትኛውም የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ያንን ታሪካዊ እውነት ሊያጣ አይችልም" ብለዋል።

ቤንጃሚን ኔታንያሁ ሐሙስ ዕለት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከአክራሪ ብሔርተኞች ጋር በመተባበር ወደ ስልጣን ተመልሰዋል።



የተባበሩት መንግሥታት የፍልስጤም ልዩ መልዕክተኛ ሪያድ መንሱር

ረቡዕ የታተመው የአዲሱ መንግሥት የመጀመሪያ መርሕ "የአይሁድ ሕዝብ በሁሉም የእስራኤል ምድር ላይ ብቸኛ እና የማያጠያይቅ መብት አለው" ሲል አውጇል። ይህም የተቆጣጠሩትን ዌስት ባንክን የሚጨምር ሲሆን በአካባቢውም ሰፈራዎችን "ለማስተዋወቅ እና ለማልማት" ቃል ገብቷል።

እአአ በ1967 እስራኤል ዌስት ባንክን እና ምሥራቅ እየሩሳሌምን ከተቆጣጠረች በኋላ ወደ 600,000 የሚጠጉ አይሁዶች አዲስ በተገነቡ 140 የሰፈራ አካባቢ ይኖራሉ።

አብዛኛው ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሰፈራውን በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ሕገ-ወጥ ቢላቸውም እስራኤል አበክራ ታጣጥለዋለች።

አዲሱ መንግሥት ያለ እስራኤል ፍቃድ የተገነቡ በዌስት ባንክ የሚገኙ 100 የሚጠጉ ግንባታዎችን ሕጋዊ ለማድረግ እና ዌስት ባንክን ለመቀላቀል ቃል ገብቷል።

በተመድ የዩናይትድ ኪንግደም ልዑካን ቃል አቀባይ ጉዳዩ ወደ አይሲጄ መቅረቡ "ሁለቱን ወገኖች ወደ ውይይት ለመመለስ ያግዛል" ብለው እንደማይሰማቸው ተናግረዋል።

ፍርድ ቤቱ "ያለ ሁለቱም ወገኖች ስምምነት የሁለትዮሽ ውዝግቡ ምንድን ነው" በሚለው ላይ ምክር እንዲሰጥ መጠየቁ "አግባብ አይደለም" ሲሉም አክለዋል።

## የፈረንጆቹ 2023 አዲስ ዓመት ትናንት በተለያዩ ሀገራት ተከብሯል

በጋዜጣው ሪፖርተር

የግሪጎሪያን ቀን አቆጣጠርን የሚከተሉት አብዛኛው የዓለማችን ክፍል አዲሱን 2023 ዓመት ተቀበሉ። በመላው ዓለም በሚገኙ ከተሞች ነዋሪዎች በብዛት ተሰባስበው በርችት ትዕይንት አዲሱን ዓመት ተቀብለዋል።

ለንደን ከተማ 12 ደቂቃዎች ከሙዚቃ ጋር የተዋሃደ የርችት ሥነ-ሥርዓት አድርጋ አዲሱን ዓመት ተቀብላለች። የከተማዋ ከንቲባ ሳዲቅ ካሃን ይህ ትዕይንት በአውሮፓ ትልቁ ነው ብለዋል።

ከኮቪድ ስርጭት ጋር በተያያዘ ከተጣሉ ክልከላዎች በኋላ በሰዎች ለአዲስ ዓመት አቀባበል በበርካታ ከተሞች በብዛት ሲሰባሰቡ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ለንደን በነበረው የአዲስ ዓመት አቀባበል በሥነ-ሥርዓቱ ከ100ሺህ በላይ ሰዎች ወደ አደባባይ መውጣታቸው ተገልጿል። በለንደኑ ርችት በሞት የተለዩት ዳግማዊት ንግሥት ኤልዛቤጥ ታውሰዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራቱ ኬንያ እና ኡጋንዳም በርችት ሥነ-ሥርዓት አዲሱን 2023 ተቀብለዋል። በካይሮ ግብጽ ደማቅ የርችት ሥነ-ሥርዓት ተከናውኗል።

ዩክሬን በ2023 ትግሏን ትቀጥላለች ያሉት ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዜሌንስኪ ናቸው። ፕሬዚዳንቱ ሀገራቸው "ለየትኛም ነገር ዝግጁ ነች" ብለዋል። በአዲስ ዓመት ዋዜማ ንግግራቸው "ይህ ዓመት የመመለስ ይሆናል" ብለዋል። "ሕዝባችን ወደ መኖሪያው የሚመለስበት፣ ወታደሮች ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚመለሱበት፣ ስደተኞች ወደ ዩክሬን የሚመለሱበት" ይሆናል ብለዋል።

የዩክሬን መዲና ኪዬቭ ጎዳናዎች ግን እንደ ተቀሩት የአውሮፓ አገራት መዲናዎች ሰዎችን አላስተናገዱም። ከተማዋ ከምሽት 5 ሰዓት በኋላ የእንቅስቃሴ ክልከላ ስለተጣለባት ጎዳናዎቿ ጭር ብለዋል። ፑቲን በበኩላቸው አዲሱን ዓመት ከወታደሮቻቸው ጋር ብርጭቆ እያጋጩ ተቀብለዋል።

የአገሪቱ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በወታደሮች ተከበው በሻምፓኝ የተሞላ መጠጥ ሲያጋጩ አሳይቷል። ያለፈው ዓመት "መልካም አጋጣሚዎችን" መፍጠራቸው እና በአዲሱ ዓመት "ሩሲያውያን እውነተኛ ነጻነትን እንቀዳጃለን" ብለዋል። ይህ አብዛኛው የዓለማችን ክፍል የሚጠቀምበት የግሪጎሪያን ቀን አቆጣጠር በሮማው ጳጳስ ጆርጅ ስምንተኛ በ1582 የተዋወቀ ነበር።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# ሴቶችን በብዙ መልኩ እየጠቀመ ያለው ማረፊያ

የ18 ዓመቷ ተማሪ ኬሪያ ጀማል በተፈጥሮዋ አካል ጉዳተኛ ሆና በመወለዷ ሁለት እጆች የሏትም። ይሁን እንጂ ማንኛውንም ነገር በእግሯ ታከናውናለች። እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ስትማር ከቤተሰቦቿ ሳትለይ በጥሩ እንክብካቤ ውስጥ ትለፍ እንጂ ከዚያ በኋላ ያለውን ትምህርቷን ግን በዚህ ሁኔታ መቀጠል አትችልም። ምክንያቱ ደግሞ ከቤተሰቧቿ ተለይታ ርቃ ልትሄድ በመሆኑ ስትመገብ የሚያግዛት እና ሌሎች ድጋፎችን የሚያደርግላት ሰው የሚያስፈልጋት በመሆኑ ነው።

ወይዘሮ አሚና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አማካኝነት የተቋቋመው የሴቶች ሆስቴል (ማረፊያ) ዳይሬክተር ሲሆኑ፤ በመምህርነትም ለ36 ዓመታት አገልግለዋል። የሴት ተማሪዎችን ጭንቀትና ጫና በሚገባ የሚረዱት ዳይሬክተሯ፤ ኬሪያንም እንዳዩዋት ምን እንደሚያስፈልጋት በመረዳት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ሴቶች ለመደገፍ ወደ ተቋቋመ ማረፊያ የምትገባበትን ሁኔታ አመቻቹላት። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ማረፊያው በተለይም ከትምህርት ጋር ተያይዞ ያሉባቸውን ፈተናዎች ከመፍታት አንጻር ከፍ ያለ ጥረት የሚያደርግ ነው። የማረፊያ ማዕከሉ ዋና ተግባር ድሬዳዋ ከተማና ዙሪያዋ እስከ 30 እና 40 ኪሎ ሜትር ድረስ ወደ ገጠር ቀበሌዎች እየወረዱ በማየት ልጃገረዶች ወደ ድሬዳዋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲመጡ ማድረግ ነው።

ከተቋቋመ 15 ዓመት ያስቆጠረው ማረፊያው ከ38 የገጠር ገበሬ ማህበራት ተውጣጥተው የሚመጡ ተማሪዎችን የሚቀበልና በትምህርታቸው የሚያግዝ ነው። በቤተሰብ የአቅም ውስንነት፣ በአካል ጉዳተኝነትና በባህላዊ ጫና ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለማድረግ አላማ አድርጎ የተቋቋመ መሆኑን የሚገልጹት ወይዘሮ አሚና፤ አካል ጉዳተኛዋን ኬሪያ በጉዳቷ ምክንያት ትምህርቷን እንዳታቋርጥ ብዙ ነገሮቿን በማደላደል ድጋፍ አድርጎላታል። ድጋፉም የመጀመሪያው ትምህርቷ እንዳይቋረጥ ሲሆን፤ ሁለተኛው ማረፊያው ተማሪዎችን የሚቀበለው ከዘጠነኛ ክፍል በኋላ



ተማሪ ኬሪያ ጀማል

ቢሆንም የሰባተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችውን እህቷን ከስሯ እንዳትለይ በማድረግ እንክብካቤዋ እንዳይቀንስ አግዟል።

እንደ ዳይሬክተሯ ማብራሪያ፤ ማረፊያው ለኬሪያ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሴት ተማሪዎች ሁሉ ልዩ እንክብካቤን ያደርጋል። በተለይም ከትምህርታቸው ጋር ተያይዞ ምንም እንዲጎልባቸው አይፈለግም። ተማሪዎቹ በቡድን፣ አልያም በተናጠል የሚያነቡበትን እድል አመቻችቶላቸዋል። ለአብነትም ኬሪያ ወደ ማረፊያው ገብታ በመጀመሪያው የትምህርት ዓመት አጋማሽ ሰባተኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀች ሲሆን፤ ከዚያም ቦታውን እየተላመደችው ስትሄድና ያለው እንክብካቤ ሲጨመርበት አንደኝነቷን ማንም ሳይነጥቃት አሁን 11ኛ ክፍል ደርሳለች። በሌላ በኩልም ከማረፊያው ውጭ የአቅም ውስንነት ያለባቸውን ወንድ ተማሪዎችንም ሙሉ ወጪያቸውን በመሸፈን ይደግፋሉ። ስለዚህም ማረፊያው የትምህርቱን ዘርፍ በመደገፍ በኩል ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው።

እንደ ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ይህንን ማረፊያ አቋቁሞ መሥራቱ ትምህርት አቋርጦ ከመሄድ፣ አግብቶ ከመቅረት፣ ችግር ሲያጋጥም አለመማርን ከመምረጥ መታደግ አስችሏል። በተጨማሪም ማረፊያው 24 ክፍሎች ያሉት ሲሆን፤ እያንዳንዱ ክፍል ስምንት አልጋዎችን በመያዝ በ15 ዓመት ጉዞው ከአንድ ሺ 500 በላይ ተማሪዎችን አስተምሮ ለቁምነገር አብቅቷል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ አሁን በማረፊያው ውስጥ አንድ መቶ 45 ተማሪዎች አሉት።

ልጃገረዶቹን ወደ ማረፍያው አስገብቶ ለማኖር ከአንሶላና ፍራሽ ጀምሮ ምግብና መጠጥ እንዲሁም በርካታ ነገሮች ያስፈልጉ ነበር። መምህርቷም ወደ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ በመሄድ የማረፊያውን መከፈት አብስረው ተማሪዎቹ አርፈው ትምህርታቸውን መማር ከጀመሩ በኋላም ደግሞ አንዳንድ ክፍተቶች አጋጥሟቸው እንደነበር ያወሳሉ። ችግሩ የድጋፍ ማነስ ጉዳይ ሲሆን፤ በዩኒሴፍ የድሬዳዋ ተወካይ የነበሩት ናይጀሪያዊት ሴት ሆስቴላቸውን እንዲጎበኙ ማድረጋቸውንም ያብራራሉ። ዩኒሴፍ በተወካዩ በኩል ከሦስት መቶ 50 ሺህ ብር በላይ እርዳታ ለ10 ዓመታት ያህል አድርጎላቸዋል። ሆኖም ድጋፉ ቋሚ ባለመሆኑ ሌላ ፈተና ነበር። ስለሆነም እንደ ትምህርት ቢሮ የተደረገው የክልሉ መንግሥት የሚደግፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ቢሆንም በጀቱ ግን አሁን ካለው የኑሮ ውድነት ጋር በእኩል የማይራመድ፤ በተለይም ከተለያዩ ወቅታዊ ቀውሶች ጋር ተያይዞ ፈተናው እንዲከፋ ያደርገዋል ይላሉ።

ዳይሬክተሯ እንደሚሉት፤ ዘርፉ የትምህርት ጉዳይ ነውና ትምህርትን ሊያግዝ የሚችል ሁሉ መጠየቅ አለበት። በዚህም ወደ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት ፓስታ፤ ሩዝ፤ ማኮሮኒና ዱቄት የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል። አንሶላና ብርድ ልብስ አላቂ እንደመሆናቸው በየጊዜው ለማሟላትም አጋዥ ድርጅቶች ይጠየቃሉም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አጋጣሚዎችን በመጠቀምም ማረፊያው የሚደገፍበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ። ምንም እንኳን በተበጣጠሰ መልኩ ድጋፍ ቢያደርጉም ችግሩን ማቅለል አዳጋች ይሆናል በመሆኑም የክልሉ መንግሥት መደገፍ ቢቻል መልካም ነው ባይ ናቸው።

በአጠቃላይ ማረፊያው በርካታ ዜጎችም በሥነ ምግባር እንዲታነፁ፤ የማሕበረሰቡን አመለካከት እንዲለውጡ አስችሏል፤ ተማሪዎች የጠለቀ እውቀት ኖሯቸው በተለያየ የትምህርት መስክ አገራቸውን እንዲያገለግሉም ረድቷቸዋል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ከዚያ በተጨማሪ ጎጂ ባህሎች ላይ ጠንከር ያለ የመፍትሄ ሀሳብን ማምጣት አስችሏል። እናም ይህ ተሞክሮ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ብቻ ሳይሆን የአገርም ሊሆን ይገባል ሲሉ ይመክራሉ።

# ስፖርት



# ዋልያዎቹ የቻን ዝግጅታቸውን ከቀናት በኋላ በሞሮኮ ይቀጥላሉ

**ብርሃን ፈይሳ**

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ከሚመራቸው ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው የአፍሪካ አገራት ቻምፒዮን ሺፕ (ቻን) ከቀናት በኋላ ይካሄዳል። ውድድሩ በአልጄሪያ ለ7ኛ ጊዜ የሚከናወን ሲሆን፤ ተሳታፊ የሚሆኑት 18 አገራትም ዝግጅታቸውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያም ካለፈው ሳምንት መጀመሪያ አንስቶ ብሄራዊ ቡድኗን በማሰባሰብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሜዳ ላይ ዝግጅቷን አጠናክራ ማከናወኗን ቀጥላለች።

ዘንድሮ ለሶስተኛ ጊዜ በዚህ ውድድር የሚካፈለው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን በመድረኩ ከምድብ ያለፈ ውጤት የለውም። ከስድስት ዓመታት በኋላም ዳግም የመድረኩ ተሳታፊ ሆኗል። በአገር ውስጥ ሊጎች ብቻ በሚካፈሉ ተጫዋቾች መካከል የሚካሄደው ይህ ውድድር ለወጣት ተጫዋቾች በርካታ እድልን ሊያስገኝ እንደሚችል ይታመናል። ከዚህ ባሻገር አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች በአውሮፓና ሌሎች አገራት ሊጎች ውስጥ የሚጫወቱ እንደመሆናቸው በዚህ ውድድር ላይ ይዘው የሚቀርቡት ቡድን ከሌላው የተለየ ነው የሚሆነው። ይኸውም እንደ ኢትዮጵያ ያሉና በርካታ የውጪ አገራት ተጫዋቾች የሌሏቸው ቡድኖችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

በመሆኑም በመድረኩ ከዚህ ቀደም ጎልቶ የሚነገር ታሪክ የሌላት ኢትዮጵያ ተወዳዳሪ ለመሆን ወደ አልጄሪያ ታቀናለች። ለዋሊያዎቹ ዋና አሰልጣኝ ውበቱ አባተ በዚህ ረገድ ኃላፊነት የሰጠው ፌዴሬሽኑ ለዝግጅቱም የተለየ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው የሚገኘው። ለቻን ዝግጅት በማድረግ ላይ የሚገኘው ቡድኑ ከአገር ውስጥ ዝግጅቱ ባለፈ ቀጣይ ዝግጅቱን በሞሮኮ የሚያደርግ ይሆናል። ቡድኑ በተያዘለት መርሃ ግብር መሰረት ከነገ በስቲያ ታህሳስ 26/2015 ዓ.ም ወደ ሞሮኮ በማቅናት እስከ ውድድሩ መዳረሻ ያሉት ስምንት ቀናት ዝግጅት እንደሚያከናውን ፌዴሬሽኑ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጠበት ወቅት አስታውቋል። በሰሜን አፍሪካዊቷ አገር አልጄሪያ የሚደረገውን ውድድር ተከትሎ የቡድን አባላቱ ከአየር ሁኔታው ጋር እንዲላመዱ በሚል ከተመረጡ አገራት መካከል አንዷ የሆነችው ሞሮኮ ናት።



**ዋልያያዎቹ የቻን ዝግጅታቸውን ከቀናት በሀላ በሞሮኮ ይቀጥላሉ፣**

ፌዴሬሽኑ የቻን ተሳታፊነቱን ተከትሎ ለተለያዩ ወጪዎች የሚሆነውን 50 ሚሊየን ገንዘብ ከመንግስት እገዛ እንዲደረግለት መጠየቁ የሚታወስ ነው። ይሁንና የተሰጠው ምላሽ ግን 28 ነጥብ 8 ሚሊየን ብር መሆኑን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል። በመሆኑም ፌዴሬሽኑ ተጨማሪ ስፖንሰሮችንና የገንዘብ ምንጮችን ከመፈለግ ባለፈ ሌሎች ወጪ ቀናሽ አማራጮችን ሲያማትር ቆይቷል። በዚህም መሰረት ከሞሮኮ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በተገባው ስምምነት ቡድኑ የመጓጓዣ ወጪውን ብቻ በመሸፈን ሌሎች የቆይታ እንዲሁም የልምምድ አስፈላጊ ሁኔታዎችን በነጻ መስተናገድ እንዲችል ተፈቅዶለታል። በተጓዳኝም በቻን ከሚሳተፈው የሞሮኮ ብሄራዊ ቡድን ጋር የአቋም መፈተሻ የወዳጅነት ጨዋታ የሚያደርግ ሲሆን፤ በእቅዱ መሰረት ሁለተኛውን የአቋም መፈተሻ ጨዋታም ከቡድኑ ጋር ለማከናወን ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝም ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

ቡድኑ በአጠቃላይ 41 አባላትን ይዞ በውድድሩ ላይ የሚሳተፍ ሲሆን፤ ከተመረጡት 28 ተጫዋቾች መካከልም ሁለቱ ተቀንሰው 26 ናቸው። ከተጫዋቾች ባሻገር የስልጠና ቡድን እና የፌዴሬሽኑ ተወካዮች ብቻ የተካተቱበት መሆኑንም ፌዴሬሽኑ አረጋግጧል። የውድድሩ ተሳታፊ ከሆነው ቡድኑ ጎን ለጎንም በሌሎች ስራዎች አገሪቷን የሚወክሉ ባለሙያዎችም አሉ። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራ የቻን ውድድር አዘጋጅ ኮሚቴ አባል በመሆን ተመርጠዋል። ፕሬዚዳንቱ ከዚህ ቀደምም በ2021 የአፍሪካ ዋንጫ ላይ ተመሳሳይ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር። የካፍ ኤሊት ኢንስትራክተር አብርሃም መብራቱም በቴክኒክ ጥናት ቡድን አባልነት የሚያገለግሉ ሲሆን፤ እአአ በ2019 እና 2021 አፍሪካ ዋንጫ ላይ ተመሳሳይ ተሳትፎ ነበራቸው። ሌላኛው ባለሙያ የፊፋ ዓለም አቀፍ ዳኛ ባምላክ ተሰማም በጨዋታ አመራርነት በቻን ውድድር እንደሚካፈሉ ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ኢንስትራክተር ባምላክ በውድድሩ ላይ ከሚሳተፉ 12 የቪድዮ ረዳት ዳኞች መካከል አንዱም ናቸው።


## ለ2ኛ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

### የግ/ጨ/ቁጥር MeU 16/2015

የመቱ ዩኒቨርሲቲ በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት ለመቱ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ህትመቶች ለሁለተኛ ጊዜ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ መስፈርቱን የምታሟሉ አቅራቢዎች እንድትሳተፉ ተጋብዛችኋል

**የጨረታው መስፈርት**

1. የ2015 ዓ.ም የታደሰና በዘርፉ አግባብነት ያለው ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለውና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል
2. ከግዥ ኤጀንሲው ወይም በክልል አቅራቢነት ምዝገባ ዝርዝር ላይ የተመዘገበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡
3. የታክስ መለያ ቁጥር (TIN number) እና ቫት ተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡
4. የጨረታ ማስከበሪያ 100,000 (አንድ መቶ ሺ) ብር ለ 118 (አንድ መቶ አስራ ስምንት) ቀናት ጸንቶ የሚቆይ በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክጋራንቲ በመቱ ዩኒቨርሲቲ ስም አዘጋጅቶ ለብቻ በፖስታ በማሸግ ከኦርጅናል ሰነዱ ጋር ማቅረብ አለበት፡፡
5. ተጫራቾቹ አሸናፊ ከሆኑ ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ ቢያንስ አስር ፐርሰንት (10%) የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና (የውልማስከበሪያ) በቅድሚያ ማስያዝ የሚችል፡፡
6. ተጫራቾች የአገልግሎቱን ዋጋ ከጨረታ ሰነዱ ጋር በተሰጠው ስፔስፍኬሽን ላይ በመሙላት የድርጅቱን ማህተምና ፊርማ በሁሉም ገጾች ላይ በማሳረፍ ኦሪጅናልና ኮፒ በማድረግ የጨረታ ማስከበሪያውን በኦሪጅናል ሰነድ ውስጥ በማስቀመጥ ሁሉንም በአንድ ትልቅ ፖስታ ውስጥ በማሸግ መቱ ዩኒቨርሲቲ ግዥ አስተዳደር ለዚህ ጨረታ ባዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚችሉ፡፡
7. የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ ለተከታታይ 15 ቀናት የሚሸጥ ሲሆን የማይመለስ 200 ብር በፋይናንስ አስተዳደር በመክፈል ከግዥ አስተዳደር ሰነድ መውሰድ ይቻላል፡፡
8. ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው በወጣበት በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በ4፡30 በመቱ ዩኒቨርሲቲ ግዥ አስተዳደር አዲሱ ህንጻ ይከፈታል፡፡ የተገለፀው ቀን የህዝባዊ በዓል ወይም እረፍት ቀን የሚሆን ከሆነ በቀጣዩ የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ላይ የሚከፈት ይሆናል፡፡
9. የሚሞላ ዋጋ ቫትን ያካተተ መሆኑ ካልተገለጸ ቫትን እንዳካተተ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
10. የጨረታው ውጤት የጨረታው ሰነድ ተገምግሞ እንዳለቀ በደብዳቤ ለያንዳንዱ ተወዳዳሪዎች ይገለፃል፡፡
11. ማንኛውም ተጫራች በመመሪያው ውስጥ የተካተቱ ህጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡
12. በሌላ ተጫራች ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፡፡
13. ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ90 (ዘጠና) ቀን ጸንቶ ይቆያል፡፡
14. የአገልግሎቱ ብዛት ሊጨምርም ሊቀንስም ይችላል፡፡
15. ዩኒቨርሲቲው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

**መቱ ዩኒቨርሲቲ**

## የስም ማስታወቂያ

ላይፍ ሴቨር ኢንተርናሽናል ቸርች (LIFE INTERNATIONAL CHURCH) የተባለ የሃይማኖት ተቋም ምዝገባ ለማድረግ ያመለከተ በመሆኑ በዚህ ስያሜ እና ዓርማ ተቃውሞ ያለው አካል ካለ በ10 ቀናት ውስጥ ወደ የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያን ካውንስል ያቅርብ፡፡

**የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያት ክርስቲያናት ካውንስል**

## የሙያና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጥፋት ማስታወቂያ

አቶ አበበ ቱጂ ጫልቺሳ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ በቀን 28/01/2014 ዓ.ም በጁኒየር ነርስ ፕሮፌሽናል (Junior Nurse Professional) በመዝገብ ቁጥር JNP =82673 RPL = 759 የወሰድኩት የሙያ እና የሥራ ፈቃድ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የጠፋ መሆኑን አሳውቆናል፡፡ ስለዚህ የባለሙያውን የሙያ እና የሥራ ፍቃድ ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት አግኝቸዋለሁ፤ በእዳ ይዤዋለሁ የሚል ተቃዋሚ ካለ እስከ 15 ቀን ድረስ ይዞ ይቅረብ፤ ባይቀርብ በምትኩ ተለዋጭ የምስክር ወረቀት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የኦሮሚያ ጤና ጥበቃ ቢሮ**

## ማስታወቂያ

ከዚህ በፊት "ወንጌል ይለውጣል አለም አቀፍ አገልግሎት" በመባል ይታወቅ የነበረው የሃይማኖት ተቋም የስም ለውጥ በማድረግ ወንጌል ይለውጣል አለም አቀፍ ቤተ-ክርስቲያን በሚል ስያሜ ለመጠራት የፈለገ መሆኑን ገልጾ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሰላም ሚኒስቴር አመልክቷል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም በሰላም ሚኒስቴር የሃይማኖት እና እምነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ይቅረብ፡፡

**ሰላም ሚኒስቴር**

## ማስታወቂያ

"እኮ የአረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች የበጎ አድራጎት ማህበር" የተባለ ማህበር ሆኖ ለመመዝገብ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ታህሳስ 29 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ በሚገኝ ህብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**